አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3565 | ቅዳሜ መጋቢት 12 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር







# ሕዝበ ሙስሊሙ

## “በረመዷን ወር የተላበሳቸውን መልካም ስነ ምግባራት ከረመዷን በኋላም ማስቀጠል አለበት”

### የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት



ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ ስታዲየም የተከበረው 1 ሺህ 447ኛው የዒድ አል ፈጥር በዓል ከፊል ገጽታ

**በይግለጡ ጓዴ**

ሕዝበ ሙስሊሙ በረመዷን ወር የተላበሳቸውን መልካም ሥነ ምግባራት ከረመዷን በኋላም ማስቀጠል እንዳለበት የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ጥሪ አቀረበ፡፡

ይህ ጥሪ የቀረበው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የ1 ሺህ 447ኛውን የኢድ አል ፊጥር በዓል አስመልክቶ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ነው፡፡

የጠቅላይ ምክር ቤቱ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት ሸይህ አብዱልከሪም ሸይህ በድረዲን በመግለጫው ላይ እንዳሳሰቡት፣ “ሕዝበ ሙስሊሙ በረመዷን ወር የተላበሳቸውን መልካም ሥነ ምግባራት ከረመዷን በኋላም ማስቀጠል አለበት” ብለዋል።

በዓሉን ስናከብር በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖቻችንን በመደገፍና በመርዳት ሊሆን ይገባል ያሉት ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንቱ፣ ሕዝበ

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## የኢድ አልፈጥር የበጎነት እሴት




6

ፎቶ- ከገፀ ድር

ቴዎድሮስ አደባባይ በሚገኘው ሜጋ አንፊ ቴአትር የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ሀይል ሲሞላ

## የበዓላቱ ተጨማሪ ድምቀት



4

ፎቶ- ከፋይል

የኮሪደር ልማቱ ለአደባባይ በዓላት ተጨማሪ ድምቀት ፈጥሯል

## የአብሮነት ድምፅ



11

ፎቶ- ከገፀ ድር

በጥዑም ዜማ የታጀበው መንዙማ ለዓለማዊ ህይወት ያለው አበርክቶ ትልቅ ነው

# ኢትዮጵያ እንድትበለጽግ

## “የሚፈለግብንን መሥዋዕትነት ሁሉ የመክፈል ኃላፊነት የእኛ ነው”

### ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ኢትዮጵያ እንድትበለጽግ የሚፈለግብንን መሥዋዕትነት ሁሉ የመክፈል ኃላፊነት የእኛ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይህን ያሉት ለዒድ አልፈጥር በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት ሲሆን፣ “ኢትዮጵያ የምታድግና የምትበለጽገው በዜጎቿ እንጂ በሌላ አይደለም ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው፣ ከሦስት አካላት ጋር ማለትም ከራሳቸው፣ ከማህበረሰባቸው እና ከፈጣሪያቸው ጋር የታረቁ ሰዎች ብርቱዎች ናቸው ብለው፣ እንደ ኢትዮጵያዊ እኛም ራሳችንን የገዛን፣ ፈጣሪን የምንፈራ እና

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



ፎቶ- ከፋይል

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለ1 ሺህ 447ኛው የዒድ አል ፈጥር በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል






# በበዓላት የሚከናወን የበጎ አድራጎት ተግባር የመደጋገፍ ባህል እያደገ መምጣቱን አመላካች ነው ተባለ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

በዓላትን ምክንያት በማድረግ የሚከናወኑ የበጎ አድራጎት ተግባራት በመዲናዋ የመረዳዳት እና የመደጋገፍ ባህል እያደገ መምጣቱን አመላካች ስለመሆኑ ተገልጿል

1 ሺህ 447ኛውን የኢድ አል-ፈጥር በዓል ምክንያት በማድረግ በከተማዋ በሁሉም ክፍለ ከተሞች በሚገኙ 28ቱም የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት አቅመ ደካሞችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንን እና ለከፋ ማህበራዊ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ ወገኖች ማዕድ የማቋደስ መርሃ ግብር ተከናውኗል፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የበዓላት የመረዳዳት እሴት የዘወትር የሕይወት መዓዛችን ይሁን!

ኢትዮጵያ የበርካታ ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት መፍለቂያ፣ የጥንታዊ ሥልጣኔና የጋራ እሴቶች መገኛ ናት። እነዚህ በዓላት ከሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓት ባለፈ፣ የተራራቁ ቤተሰቦች የሚገናኙባቸው፣ የሻከሩ ወዳጅነቶች የሚታደሱባቸውና የማኅበራዊ ትስስር ድልድዮች የሚጠናከሩባቸው አጋጣሚዎች ናቸው። በተለይም የኢኮኖሚ አቅማቸው የፈቀደላቸው ወገኖች ለሌላቸው በማካፈል፣ በዓሉን ሁሉም በደስታ እንዲያሳልፈው የሚያደርጉበት የቆየና የላቀ የቸርነት ልማድ የሀገራችን መገለጫ ነው። ትናንት የተከበረው የዒድ-አልፈጥር በዓልም ይህንኑ ድንቅ እሴት በደመቀ ሁኔታ የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ ሙስሊሙ ማህበረሰብ በጾም የታነጸ ማንነቱን ለተቸገሩት በመዘርጋትና “ዘካተል-ፈጥርን” በማውጣት ፍጹም ሰብአዊነቱን እያሳየ ይገኛል።

የእስልምና አስተምህሮ ለመረዳዳትና ለምጽዋት የሚሰጠው ስፍራ እጅግ ከፍተኛ ነው። ዒድ-አልፈጥር ከአንድ ወር የረመዳን ጾም በኋላ የሚመጣ በዓል በመሆኑ፣ አማኙ ራሱን ከራስ ወዳድነት አርቆ ለሌሎች እንዲኖር አቅም ይሆነዋል። ቁርዓናዊ መመሪያዎችና የነቢዩ መሐመድ ሱናዎች እንደሚያስተምሩት፣ ጎረቤቱ ተርቦ እርሱ ጠግቦ የሚያድር አማኝ ሙሉነት የለውም። ይህ አስተምህሮ በበዓል ዕለት ብቻ ሳይሆን፣ አማኙ በቆይታው ሁሉ ደካሞችን እንዲያነሳ፣ ብቸኞችን እንዲያስታውስና የኢኮኖሚ ፍትሐዊነትን እንዲያሰፍን የሚመክር ነው። በመሆኑም በዒድ አልፈጥር የሚታየው መረዳዳት የዚህ ጥልቅ መንፈሳዊ ትምህርት ፍሬ እንጂ ድንገታዊ ክስተት አይደለም።

ኢትዮጵያውያን ለዘመናት የገነቡት የመረዳዳት ባህል በዓለም አቀፍ ደረጃ አርአያ ሊሆን የሚችል ነው። ችግር ሲመጣ በጋራ መቆም፣ ደስታን በማካፈል ማድመቅና የተቸገሩትን ማገዝ በደማችን ውስጥ ያለ የቆየ ማንነታችን ነው። ይህ የመረዳዳት ባህል እንደ ማኅበረሰብ እርስ በርስ የሚተሳሰብና በችግር ጊዜ የማይበገር ጠንካራ ሕዝብ ለመፍጠር ያለው ሚና የማይተካ ነው። አንድ ማኅበረሰብ በቁሳዊ ብልጽግና ብቻ ሳይሆን፣ በሥነ- ልቦናዊ ትስስርና በሰብአዊ ርኅራኄ ሲገነባ የሀገሩን ሰላምና መረጋጋት በጽኑ መሠረት ላይ ያቆማል። መረዳዳት የሕዝብ አንድነት ዋነኛ የትስስር ምሰሶ ነው።

ይሁን እንጂ ይህ በበዓላት ወቅት የሚታይ እጅግ የሚናፈቅና የሚደነቅ የመረዳዳት ተግባር በዓላትን ብቻ ጠብቆ የሚመጣ ወቅታዊ ክስተት ሆኖ መቅረት የለበትም። ለዒድ ተብሎ የተዘረጋው እጅ፣ ነገም ለዕለት ተዕለት ኑሮ መዘርጋት ይኖርበታል። ችግርና ረሃብ፣ ሕመምና ስደት በዓላትን ጠብቀው የሚመጡ ክስተቶች አይደሉም። በመሆኑም በበዓል ወቅት የምናሳየውን ልግስና እና ርኅራኄ ወደ ዘወትራዊ የሕይወት ልምዳችን መለወጥ የዜግነትና የሃይማኖታዊ ግዴታችን ሊሆን ይገባል። እያንዳንዱ ዜጋ በየዕለቱ የቻለውን ያህል ለሌሎች ማካፈልን ባህል ካደረገ፣ በከተማችንም ሆነ በሀገራችን የከፋ ችግር ውስጥ የሚወድቅ ዜጋ አይኖርም።

በጥቅሉ በዒድ አልፈጥር ሙስሊሙ ማህበረሰብ የሚያሳየው የመረዳዳትና የመተሳሰብ ተግባር ለሁላችንም ትልቅ ትምህርት ሊሆነን ይገባል። በዓላት የፍቅርና የአንድነት መድረክ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በእነዚህ ቀናት የምናሳየው የደግነት ስሜት የዘወትር ተግባራችን እንዲሆን ቆርጠን መነሳት ይጠበቅብናል። በዓላት ያልፋሉ፤ የሰዎች ፍላጎትና ችግር ግን ይቀጥላል። በመሆኑም የመረዳዳት ልምዳችንን ወቅታዊ ሳይሆን ዘወትራዊ በማድረግ፣ ፍቅርና ሰብአዊነት የነገሡባት ኢትዮጵያን በጋራ እንገንባ። እንኳን ለዒድ-አልፈጥር በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ደግነት እንደ ክረምት ዝናብ ወቅት ጠብቆ ሊመጣ አይገባም!

**በቸርነት ዋለልኝ ከአራብሳ**

ኢትዮጵያውያን ለዘመናት የዘለቁ፣ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ድንቅ ቅርሶች ባለቤቶች መሆናችን የአደባባይ ምስጢር ነው። ከእነዚህ ቱባ ባህላቶቻችን መካከል ደግሞ መደጋገፍና መረዳዳት እንደ ማገር ሆነው ማህበራዊ ህይወታችንን አጽንተውታል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ይህ እሴት ከራስ ስነ-ልቦና ጋር የሚያስታርቅ፣ ከፈጣሪም ጋር ያለንን መስተጋብር የሚያጠነክር የጽኑ ማንነታችን መገለጫ ነው ብዬ አምናለሁ። ሆኖም ግን፣ ዛሬ ላይ ቆም ብለን መጠየቅ ያለብን አንድ ትልቅ ጥያቄ አለ፤ ይህም በጎነታችን እንደ ክረምት ዝናብ ወቅት ጠብቆ የሚመጣና የሚሄድ ነው? ወይስ የሁልጊዜ ተግባራችን መሆን አለበት? የሚል ነው፡፡

በሀገራችን በአፅዋማትና የበዓላት ወቅቶች የመረዳዳት መንፈስ የሚነቃቃባቸው ናቸው። ሆኖም ጥያቄው፣ ‘ወቅቱ ምን ያዘናል? ሳይሆን እኛ ለወቅቱና ለወገናችን ምን ይዘናል?’ የሚለው መሆን አለበት። የአፅዋማትና የበዓላት ወቅት ማለፉ የማይቀር ነው፤ ትልቁ ቁምነገር ግን በእነዚህ ወቅቶች የምናሳየው ርህራሄና መደጋገፍ በውስጣችን ምን አይነት ዘላቂ ለውጥ አምጥቶ ያልፋል? የሚለው ነው።

ከመቀበል ይልቅ መስጠት የሚያስገኘውን ደስታ የምንረዳው፣ ደግነትን በጊዜ ገደብ ሳንገድብ በቋሚነት ስንለማመደው ብቻ ነው። ስለዚህ ጾም ከምግብ መታቀብ ብቻ ሳይሆን፣ ለተራቡት መድረስና ለተገፉት መጠለያ መሆን ነው። ይህ ደግሞ ዓመቱን ሙሉ የሚቀጥል የሕይወት ዘይቤ ሊሆን ይገባል።

ረዳት ለሌላቸው ማገዝ፣ የታመሙትን መጠየቅና የተራቡትን ማብላት በሁሉም የኃይማኖት አስተምህሮዎች የሚበረታታ ተግባር ነው። ነገር ግን ብዙ ጊዜ የምናየው እንቅስቃሴ በጾም ወቅቶች፣ በበዓላት ሰሞን ወይም በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ ብቻ የተገደበ መሆኑ ያሳስባል። ሰብዓዊነትና የዜግነት ኃላፊነት የቀን መቁጠሪያን ተከትሎ የሚመጣ ዘመቻ እና ወቅታዊ አጀንዳ ሊሆን አይገባም ባይ ነኝ። ችግር ቀጠሮ ይዞ ስለማይመጣ፣ የእኛም ምላሽ ወቅትን ጠብቆ የሚመጣ መሆን የለበትም።

መደጋገፍ ሲባል ከቁሳዊ እርዳታ ባለፈ፣ በዙሪያችን ላሉት ሰዎች ሞራላዊና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ መስጠትንም ይጨምራል። ከመቀበል ይልቅ መስጠት የሚያስገኘውን ሰላምና ደስታ የሚረዳ ትውልድ ለመፍጠር ትልቅ ስራ ይጠብቀናል ብዬ አስባለሁ። ስለሆነም፤ መረዳዳትና መደጋገፍ የወቅታዊ ዘመቻዎች ውጤት ሳይሆን የዕለት ተዕለት ማንነታችን መገለጫ ሊሆን ይገባል።

ይህ እሴት በትውልድ ዘንድ ስር እንዲሰድ የሚዲያ ተቋማት፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የትምህርት ተቋማትና ከሁሉም በላይ ደግሞ ቤተሰብ የዚህ እሴት ጠባቂ ሊሆኑና የየድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል ባይ ነኝ። ኢትዮጵያዊውን የመደጋገፍ ትውፊት ከወቅታዊነት አውጥተን የዘላቂ ህይወታችን መመሪያ ልናደርገው ይገባል። ደግነት እንደ ወንዝ በቋሚነት የሚፈስ የሰብዓዊነታችን መገለጫ እንዲሆን የዘላቂ ህይወታችን መመሪያ ልናደርገው ይገባል፤ እናም እያንዳንዳችን በየቤታችንና በየአካባቢያችን ልንሰራ ይገባል ባይ ነኝ።

እንዲሁም ደግነት እንደ ክረምት ዝናብ በድንገት መጥቶ የሚጠፋ ሳይሆን፣ እንደ ወንዝ በቋሚነት የሚፈስ የሰብዓዊነታችን መገለጫ እንዲሆን እያንዳንዳችን በየቤታችንና በየአካባቢያችን መስራት ይኖርብናል። መረዳዳት የሁልጊዜ ባህላችን ይሁን! ጾምም ሆነ በዓላት የሚያልፉት ለእኛ መልካምነትን አስተምረው መሆን አለበት።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ፋንታነሽ ተፈራ
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ሄለን ጥላሁን

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# በበዓላት ... ከገጽ 1 የዞረ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በሚገኘው 6ኛው እና በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ በሚገኘው 21ኛው የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት በመገኘት ማዕድ በማቋደስ እንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በወቅቱ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች፣ በመዲናዋ የመረዳዳት እና የመደጋገፍ ባህል እያደገ መሆኑን አንስተው፣ በዓሉን ምክንያት በማድረግ የተከናወነው የበጎ አድራጎት ተግባርም ይህንን የሚያጠናክር መሆኑን ገልፀዋል።

ከንቲባ አዳነች አክለውም፣ “ያደረግንላችሁን ጥሪ በመቀበል በማዕከላቱ እየመገባችሁ ለምትገኙ ባለሀብቶች፣ አጋሮች እና አስተባባሪዎች በተጠቃሚዎቹ ስም ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በዓሉ ደስታና አብሮነት የሚጎለብትበት ይሁንልን” ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ 1 ሺህ 447ኛውን የዒድ አል ፈጥር በዓል ምክንያት በማድረግ ማዕድ አጋርተዋል

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች በዓሉ ደስታና አብሮነት የሚጎለብትበት እንዲሆንም ተመኝተዋል።

ማዕከላቱ በዐቢይ ጾም እና በረመዳን ወቅትም ጭምር ለጾመኞች እንደየ እምነታቸው የአፍጥር እና የፆም ምግብ አገልግሎት ሲሰጡ መቆየታቸው ተጠቁሟል፡፡

# ኢትዮጵያ ... ከገጽ 1 የዞረ

ለማህበረሰብ ሰላምና እድገት የምንጨነቅ መሆን አለብን ሲሉ አክለዋል።

ኢትዮጵያ ዜጎችዋ ሲገነቡ ትገነባለች ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ ዜጎችዋ ሰላም ሲሆኑ ሰላም እንደምትሆንና ዜጎችዋ ሲስማሙ የብልጽግና ጉዞዋ እንደሚሰምር በመልዕክታቸው አስፍረዋል።

አያይዘውም የኢትዮጵያም መበልጸግ የሌላ ሳይሆን የእኛ መበልጸግ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ እንድትበለጽግ የሚፈለግብንን መሥዋዕትነት ሁሉ የመክፈል ኃላፊነት የእኛ ነው። የእኛ ልፋት ከዛሬ አልፎ ለትውልድ ይተርፋል። ሀገር መውደዳችን የሚታወቀውና መልካም ዜግነታችን የሚገለጠው በሥራችን ነውም ብለዋል።

“ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.)፣ ‘ምርጥ ሰዎች ማለት ሌሎችን ለመጥቀም የበረቱ ሰዎች ናቸው’ ብለው ያስተማሩትም ለዚህ ነው። ይሄን የዒድ አልፈጥር በዓል እነዚህን መልካም ዕሴቶች እያሰብን፣ ሦስቱን ጤናማ መሥመሮችንም እያጸናን እንድናከብረው አደራ እላለሁ” የሚል ጥሪ አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በሌላኛው መልዕክታቸው፣ ከራሳቸው ጋር ሰላም ያጡ አካላት የማኅበረሰቡን ሰላም እንዲረብሹ ልንፈቅድላቸው አይገባም ይላሉ። አያይዘውም፣ “ከረመዳን ዕሴቶች ጋር የተጣሉ ሰዎች ዘመኖቻችንን እንዲረብሹ ልንፈቅድላቸው አይገባም። በዐሥራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መኖር ቀድሞ መገኘት ነው። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እንደ ዐሥራ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን መኖር ግን መረገም ነው” በማለት በአጽንኦት ተናግረዋል።

አክለውም፣ መግደል፣ ማገት፣ የገበሬውን እርሻ ማቃጠል፣ ሴቶችን መድፈር፣ ማኅበራዊ ተቋማትን መመዝበር፣ ቅርስና ታሪክን ማበላሸት፣ ጠመንጃን የሁሉም ነገር መድኃኒት አድርጎ መውሰድ፣ እነዚህ ሁሉ ከ800 ዓመታት በፊት ያለፉ የሰው ልጅ ጠባያት ስለመሆናቸውም ገልፀዋል።

በሕዝበ ሙስሊሙ ዘንድ ዒድ አልፈጥር የበረከት በዓል ተደርጎ እንደሚታመን የገለፁት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ረመዳንም የአላህ (ሱ.ወ) ደግነት የሚገለጥበት፣ ውድ ስጦታዎችን ለሰው ልጆች የሰጠበት ወር ነው። ቁርአን ወደ ምድር የወረደበት፣ ጀሃነም ተዘግቶ የጀነት በሮች የሚከፈቱበት፣ ሁሉም እንደ እምነቱ ጽናትና እንደ አላህ (ሱ.ወ) እዝነት ምንዳዎችን የሚያገኝበት ወቅት በመሆኑ ሕዝበ ሙስሊሙ ዘወትር የረመዳንና ዒድ አልፈጥርን መምጣት በጉጉት ይጠብቃል ይላሉ።

በዒድ አልፈጥር ከፈጣሪ በረከት የሚቸራቸው የረመዳንን ወር በፆምና በዱዓ ያሳለፉት ናቸው፤ በበዓሉ መምጣት የሚደሰቱትም ረመዳንን በመልካም ተግባር ለማሳለፍ የበረቱ ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በተቀደሰው ወር ከክፋት የተቆጠቡ፤ ለድኾችና አቅመ-ደካሞች ዘካት የሰጡ፤ የበደሏቸውን ይቅር ለማለት የደፈሩ በሐሴትና በመንፈሳዊ ኃይል ተሞልተው ለዒዱ ይደርሳሉ። በተቃራኒው ለዱዓ የሰነፉና ለመስጠት የሰሰቱ ከፈጣሪ በረከት አያገኙም ሲሉ በመልዕክታቸው አስፍረዋል።

አያይዘውም በቀጣይ ግንቦት ወር ላይ የሚካሄደውን ምርጫ አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክት፣ ከፊታችን ግንቦት ላይ የሚካሄደው ምርጫ ሀገራችንን የዴሞክራሲ ድል የምትቀዳጅበት፣ ወደ ቀጣይ ብሩህ ዘመንዋ የምትሸጋገርበት በር ነው። እንደ ሀገር ለዓመታት ዴሞክራሲን ስንናፍቅ ኖረናል፤ ጉዞአችን አልጋ በአልጋ አልነበረም። ነገር ግን ከፈተና በኋላ በረከት፣ ከብርታት በኋላ ሐሴት እንዳለ ከረመዳን ጾምና ከዒድ አልፈጥር በዓል እንማራለን ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም፣ መልካም የዘራ ሰው መልካም ምርት እንደሚያጭድ ሁሉ፤ እሾክ የዘራውም አሜኬላ ያጭዳል። ስለተመኘን ብቻ አሜኬላው በመልካም ሰብል አይለወጥም። በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊ ጉዳዮች ውስጥ ዘርና ምርት የተቆራኙ ናቸው። ስለ ዴሞክራሲም ስናስብ ይሄንን ሐቅ መዘንጋት የለብንም። የምንገነባው ሕጋዊና ሕዝባዊ መንግሥት የሚወሰነው በቅድመ ምርጫ ተሳትፎአችን ልክ ነው ሲሉም አስረድተዋል።

ተሳትፎአችን ከጠየመ ዴሞክራሲያችንም ይጠይማል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ደካማ ተሳትፎ አድርገን ጠንካራ ዴሞክራሲ ለማዋለድ መመኘትም ሞኝነት ነው። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በባዶ መሬት አይበቅልም፤ በግጭትና ሥርዓት አልበኝነትም አይገነባም። ይልቁንም ስክነትን፣ ለትብብርና ቅንጅት ልብን ክፍት ማድረግን፣ በጨዋታው ሕግ መመራትን ይጠይቃልም ብለዋል።

አክለውም ረመዳን ቤተሰብ የሚገናኝበት፣ ሕሊና የሚሰበሰብበት፣ ሰውነት የሚገራበት እና መንፈስ የሚቀናበት ወር ነው። ዒድ አልፈጥር ደግሞ የሰውን ልጅ ጤናማ ግንኙነቶች የሚያመለክት በዓል ነው። የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር፣ ከራሱ ጋር እና ከወገኑ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ጤናማ ካልሆነ ጠቅላላ ሕይወቱ ጤናማ አይሆንም። በረመዳን ወቅት ጾሙ ሰዎችን ከራሳቸው ጋር ያገናኛቸዋል፤ ሰላትና ዱአ ከፈጣሪያቸው ጋር ያገናኛቸዋል፤ አፍጣርና ዘካት ደግሞ ከማኅበረሰቡ ጋር ያገናኛቸዋል። ኢትዮጵያውያን ጤናማ ሕይወትን መምራት እንድንችል እነዚህን ሦስቱን ጤናማ ማድረግ አለብን በማለት ገልፀዋል።

ሰው ከፈጣሪው እና ከራሱ ጋር ያለው ግንኙነት ጤናማ ካልሆነ ለማኅበረሰብም ለሀገርም ጠንቅ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ሰው ከራሱ ጋር እየተጋጨ ከኖረ ከሁሉም ጋር ይጋጫል ብለዋል። ዛሬ ጦርነትን ባህል፣ ዝርፊያን ልማድ፣ ጥፋትን ዕሴት፣ ውድመትን ክብር አድርገው የሚኖሩት ሰዎች የመጀመሪያው ችግራቸው ከፈጣሪያቸውና ከራሳቸው ጋር አለመስማማት ነው። ውስጣዊ ባሕርያቱ ያልተስማሙለት ሰው ከማንም ጋር አይስማማም ሲሉ በመልዕክታቸው አስፍረዋል።

ሰው ከፈጣሪውና ከራሱ ጋር ከተስማማ፣ ከማንም ጋር መስማማት ይችላል፤ ከእንስሳትም ጋር ሳይቀር። “ለድንቢጥ እንኳን ቢሆን የራራ ሰው፤ በፍርድ ቀን (ቂያማህ) አላህ ይራራለታል” ሲሉ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ያስተማሩት ለዚህ ነው። የእስልምና ዋናው መሠረቱ ሰላም የሆነው ለዚህ ነው። ሰላም ማለት ከራስና ከአካባቢ ጋር በጤናማ ግንኙነት ለመኖር መቻል ስለመሆኑም አስረድተዋል።

የዘንድሮውን የዒድ በዓል ስናከብር በዓለማችን ስለ ሰላም የሚነገረውን ያህል የዓለም ሕዝቦች በሰላም መኖር ለምን አልቻሉም ብለን እንጠይቅ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የግጭትና የጦርነት ድንጋይ እየደጋገመ ለምን ይመታናል? ከአዛኝ ይልቅ ገዳይን እንደ ጀግና የሚያየው ልምምዳችን ለምን ገናና ሆነ? የሰው ልጅ ከግጭትና ከጦርነት ያተረፈው ድህነትና ኋላቀርነት መሆኑን እያየን ለምን አልተማረንም? ሠልጥኗል በምንለው ዓለም የሚኖሩ ወገኖቻችን እንዴት ግጭትንና ጦርነትን የሚያበረታቱ ሆኑ? ይህ ትውልድ እነዚህን ጥያቄዎች በሚገባ አጢኖ ምላሽ ሊያገኝላቸው ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ሕዝበ ... ከገጽ 1 የዞረ

ሙስሊሙ በረመዷን ወር የተላበሳቸውን መልካም ሥነ ምግባራት ከረመዷን በኋላም በማስቀጠል ዒዱን በአብሮነት፣ በመረዳዳትና በደስታ ሊያከብር እንደሚገባም አሳስበዋል።

የጠቅላይ ምክር ቤቱ የአስተዳደር ጉዳዮች እና የተቋማት ልኅቀት ዘርፍ ምክትል ፕሬዝዳንት ኡስታዝ ተምኪን አብዲላሂ በበኩላቸው፣ በኢስላማዊ አስተምህሮ መሠረት በኢድ ቀንም ሆነ ከኢድ በኋላ እኛ በልተን እያደርን ጎረቤቶቻችን ተርበውና ተከፍተው ሊውሉና ሊያድሩ አይገባም ብለዋል።

በተያያዘም የታላቁ አንዋር መስጂድ ኢማም ሐጂ ጠሃ ሀሩን በትናንትናው ዕለት የ1 ሺህ 447ኛው የኢድ አል ፊጥር በዓል አከባበር እና የሶላት ሥነ ሥርዓት በአዲስ አበባ ስታዲየም በተከናወነበት ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት፣ ኢትዮጵያ የሰላም፣ የፍቅርና የአንድነት ሀገር እንድትሆን እያንዳንዱ ዜጋ በአብሮነት መቆም እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

በዓሉ በጁምዓ ቀን መዋሉ ልዩ በረከት እንዳለው የጠቆሙት ሐጂ ጠሃ፤ ለሀገር ሰላምና መረጋጋት ዱዓ በማድረግና የሸዋልን ስድስት ቀናት በመጾም መንፈሳዊ ጥንካሬን ማሳደግ እንደሚገባም አባታዊ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ትናንት የ1 ሺህ 447ኛው የኢድ አል ፊጥር በዓል አከባበር እና የሶላት ሥነ ሥርዓት በአዲስ አበባ ስታዲየምና በዙሪያው በሚገኙ ጎዳናዎች በታላቅ ድምቀት ሲከበር የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ፣ ሌሎች የእምነቱ አባቶች፣ የውጭ ሀገር አምባሳደሮች እንዲሁም በርካታ የእምነቱ ተከታዮች ተገኝተዋል፡፡

# የበዓላቱ ተጨማሪ ድምቀት

• በአዲስ አበባ ከተማ የተከናወነው የኮሪደር ልማት ስራ እንደ ኢድ አልፈጥር ላሉ በዓላት ድርብ ድምቀት እንደሚሰጥ ተመላክቷል

በመለሰ ተሰጋ

አዲስ አበባ እንደ መስከረም ፀሐይ ደመናውን ጥሳ፣ እንደ አደይ አበባ ውበትን ተላብሳ እንደ ንስርም በፍፁም ታድሳ የብዙዎችን ቀልብ እየሳበች እንደሆነ ዓለም አቀፍ ተቋማት ሳይቀሩ በመመስከር ላይ ናቸው፡፡ ለዚህም በቅርቡ የኢኮኖሚስት ኢንተለጀንስ ዩኒት "የአፍሪካ ከተሞች በ2035" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ ነሐሴ 23 ቀን 2024 ይፋ ያደረገውን መረጃ በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

በዚሁ መረጃ መሰረት አዲስ አበባን ጨምሮ ስድስት ከተሞች በ2035 ወደ ሜጋ ከተማነት ያድጋሉ። ይህ ግምት የተሰጣቸው አዲስ አበባ፣ ሪዮ ዲጄኔሮ፣ ዳሬሰላም እና ኪጋሊ ናቸው።

"በርግጥም ስለአዲስ አበባ አስገራሚ ለውጥ ለመናገር ምስክር አያሻም፤ ምክንያቱም ከተማዋ እንደስሟ አበባ እየሆነች ስለመምጣቷ የተመለከታት ሁሉ ምስክር ነው፡፡" ይላሉ የመዲናዋ ነዋሪ አቶ አህመድ ከማል፡፡ በመዲናዋ ከ35 ዓመታት በላይ እንደኖሩ የነገሩን አቶ አህመድ እንደሚሉት ከተማዋ ቀደም ባሉት ዘመናት ነግዶ ለማትረፊያ እንጂ ያን ያህል ለመኖሪያ ምቹ እንዳልነበረች ተናግረዋል፡፡

የዚህን ምክንያት ሲያብራሩም፣ ንፅህናቸውን ያልጠበቁ መንገዶችና መንደሮች በብዛት ከመኖራቸውም በላይ በአንዳንድ አካባቢዎች ክረምት በመጣ ቁጥር አሊያም ሙቀቱ በሚያይልባቸው ወቅቶች ወረርሽኞች ጭምር ይከሰቱ እንደነበር አስታውሰው አሁን በከተማዋ እየተከናወነ ባለው ልማት እነዚህ ችግሮች እየተፈቱ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

አሁን ከተማዋ ለንግድ ብቻ ሳይሆን ለመኖሪያም የምትመረጥ፣ ጎዳናዎቿ የሚያምሩ ውብ ከተማ ሆናለች፡፡ በዚህ ላይ እንደ ኢድ አልፈጥር የመሳሰሉ በዓላትን ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ ሲያከብር ከህብረ ቀለማቱ ውበት ጋር የተዳመረ ገፅታዋ ጎልቶ ሲወጣ እጅጉን ታምራለች ይላሉ አቶ አህመድ፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ በተለምዶ ባሻ ወልዴ ተብሎ የሚጠራ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ፎዚያ አህመድ በበኩላቸው፣ የአዲስ አበባ ውበት ነግቶ በጠባ ቁጥር አዲስ እየሆነ ነው ይላሉ፡፡ መንገዶች ከመዋባቸው የተነሳ አንዳንድ የማውቃቸው ስፍራዎች ጭምር ግር እያሉኝ መጥተዋል የሚሉት ወይዘሮ ፎዚያ፣ ይህን መሰል ለውጥ ከእኛ ባሻገር ለልጆቻችን እና ለልጅ ልጆቻችን ትልቅ ሀብት እንደማስቀመጥ ነው፡፡ በተለይም እንደ ኢድ አልፈጥ ያሉ ኃይማኖታዊም የሆኑ ሌሎች በዓላትን በአደባባይ ወጥተን ስናከብር የከተማዋ አሁናዊ ገፅታ ደስታችንን አይረሴ ያደርጉታል ብለዋል፡፡

የፎክሎር ባለሙያው አቶ ግዛው ማሞ እንደሚሉት፣ በኢትዮጵያ የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት በዛ ያሉ ቢሆኑም በተለይ እንደ ኢድ አልፈጥር ኃይማኖታዊ በዓላት በበርካታ የሀገሪቱ ክፍሎች በድምቀት የሚከበሩና የማህበረሰቡን እሴት በጉልህ የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡



ፎቶ- ከፋይል

የኮሪደር ልማቱ ለአደባባይ በዓላት ተጨማሪ ድምቀት ፈጥሯል

በእነዚህ በዓላት የሚታደሙ ኢትዮጵያውያን በተለይ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች እና አደባባዮች ሲታዩ ህብረ ብሔራዊነት ነፍስ ዘርቶ የሚደምቅበት፣ የማህበረሰቡ የተለያዩ ውብ ኃይማኖታዊ ስርዓቶች እና ባህላዊ አልባሳትና ጭፈራዎች በመዲናዋ አደባባይ የኢትዮጵያውያንን መልክና ልክ አጉልተው ሲያሳዩ በርካታ ጎብኝዎችን ቀልብ ይስባሉ፡፡

አዲስ አበባ እንደ አዲስ ውበቷ እየፈካ፣ ጎዳናዎቿ እንደ ፅጌሬዳ አበባ የሚያሳሱ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ ታዲያ በእነዚህ ውብ ጎዳናዎችና አደባባዮች ላይ እንደ ኢድ አልፈጥር የመሳሰሉ ኃይማኖታዊ በዓላት ሲከበሩ ለከተማዋ ተጨማሪ ውበትን ለበዓላቱ ደግሞ ድርብ ድምቀትን ይሰጣሉ፡፡

ኃይማኖታዊም ሆነ የህዝብ በዓላት ህዝቡ በክት ልብሱ ደምቆ፣ መልካም መንፈስን ታጥቆ እና ከቤቱ ወጥቶ የሚያከብራቸው በዓላት በመሆናቸው በህብረ ቀለማት ያሸበረቁ ናቸው፡፡ ታዲያ የበዓላቱና የአደባባዮቹ ድምቀት አብሮ ሲደመር ለከተማዋ ትልቅ ፍካትን ይፈጥራሉ፡፡ የማህበረሰቡም መልካም እሴቶች እንዲጎለብቱም ዕድል ይሆናሉ ይላሉ የፎክሎር ባለሙያው አቶ ግዛው ማሞ፡፡

የኢትዮጵያውያን ውብ ባህላዊ እሴቶች እንዲህ ደምቀው በአደባባይ ሲታዩ፣ ለሌላው ዓለም የህዝቡን መልካም ገፅታ እንዲሁም የሀገርን ሁለንተናዊ ከፍታ ያሳያሉ፡፡ እየለማ ያለው ግዑዝ የሆነው ቦታ ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡም ነባር እሴት በመሆኑ በማህበረሰባዊ፣ በኢኮኖሚያዊም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ያለው ፋይዳ ከፍ ያለ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል፡፡

አዲስ አበባ አስደናቂ ለውጥ እያስመዘገበች ያለች ሲሆን፣ ለዚህ ለውጥ በዋቢነት የሚነሳው የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት ነው። ይህም የከተማዋን አካላዊ ገጽታ በመቅረጽ ብቻ ሳይሆን ኃይማኖታዊና ህዝባዊ በዓላት በሚያምሩ ጎዳናዎች እንዲከበሩና ከፍ ብለውም እንዲታዩ በር የከፈተ እንደሆነም ገልፀዋል፡፡

የኮሪደሩ ልማቱ፤ የአዲስ አበባን መሠረተ ልማት ለማዘመን እና የበለፀገ የባህል ቅርሶቿን በመጠበቅ ላይ ያለመ የከተማ ፕላን ፕሮጀክት ስለመሆኑ የገለፁት አቶ ግዛው ይህም ልማት አዳዲስ መንገዶችን፣ መናፈሻዎችን እና የህዝብ ቦታዎችን መገንባትን ያጠቃልላል። ከመሰረተ ልማት ባሻገርም ከተማዋ ኃይማኖታዊም ሆነ ባህላዊ በዓላትን በከፍታቸው ልክ የማስተናገድ አቅም እንዲኖራት አድርጓልም ብለዋል፡፡

ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ የበለጠ እርካታን ከመፍጠሩ በላይ ለባህልና ወጉ ያለው ፍቅርና አክብሮት እንዲጎለብት ያደርጋል፡፡ ለአብነትም በኢድ አልፈጥር በዓል የመዲናዋ የእስልምና እምነት ተከታዮች በተለያዩ አልባሳት እና ኃይማኖታዊ ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ ተውበው እንደሚደምቁ አስታውሰው፣ አሁን ደግሞ የመዲናዋ መንገዶች በኮሪደር ልማት እጅግ በመዋባቸው በዓሉ ከመቼውም ጊዜ ለየት ባለ መልኩ ማራኪ ገፅታ እንደሚኖረውም ተናግረዋል፡፡

ኃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት ሰዎች ልባቸውንም፣ ልብሳቸውንም አፅድተው በህብረት የሚያከብሯቸው በመሆኑ ንፁህ ስፍራዎችም ያስፈልጓቸዋል፡፡ የኮሪደር ልማቱ ያስገኘው አንዱ በረከትም ለእነዚህ በዓላት ምቹ ማክበሪያ ቦታዎችን ነው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡን ስጋና ነፍስ ለማስደሰት ትልቅ አቅምን ፈጥሯል። ይህም ለከተማዋ ተጨማሪ ውበት ለበዓላቱም አይረሴ ድምቀት ነውም ብለዋል፡

አክለውም ማህበረሰቡ በእነዚህ ስፍራዎች የአደባባይ በዓላትን ያለምንም መጨናነቅ በፍፁም ደስታና ውበት ሲያከብር ሀገራዊ ኩራት እንዲሰማው ይሆናል፡፡ የተሰራው ልማት ለእርሱ እንደሆነም በሚገባ እንዲረዳው፣ ልማቱንም እሴቶንም እንዲጠብቅና እንዲያከብር ያነሳሱታል፡፡

ወጣት እንድሪስ ጀማል በበኩሉ በኮሪደር ልማቱ ውብ ገፅታን የተላበሱት አዲሶቹ ቦታዎች ዝም ብለው የተገነቡ ሳይሆኑ ባህላችንን የምናከብርባቸው፣ ሰዎች ተሰብስበው የሚዝናኑባቸው መሆናቸውን ስለመታዘቡም አጫውቶናል፡፡ "የአደባባይ በዓላት ከመንፈሳዊ አስተምህሮው ባሻገር የባህላችን ማሳያዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም የኮሪደር ልማቱ በዓላቱን ከመቸውም ጊዜ በላቀ መልኩ እንድናከብራቸው የሚያስችለን ነው" ብሏል፡፡

የፎክሎር ባለሙያው አቶ ግዛው ማሞ እንደሚሉት፣ በከተማዋ ተከናወነው ኮሪደር ልማት ባህልን የጠበቀ የዘመናዊ ጉዞን እየተከተለች መሆኑንም የሚያመላክት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከእራሱ ጋር የታረቀ፣ እሴቱንና ወጉን የጠበቀ ማህበረሰብን ለመገንባት ትልቅ ጉልበት አለው፡፡

ከተማዋ ለሕዝባዊ በዓላት አዲስና ደማቅ ቦታዎችን በመፍጠር መሰረተ ልማቷን ከማዘመን ባለፈ ባህላዊ ማንነቷን እያጠናከረች ትገኛለች። የከተማዋ መሠረተ ልማት ማሻሻያዎች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገቷን ከመደገፍ ባለፈ ለባህላዊ ቅርሶቿ አዲስ አድናቆት እንዲኖራት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። በነዚህ በታደሱ ቦታዎች ላይ ተጨማሪ በዓላት እና ህዝባዊ ዝግጅቶች ሲካሄዱ፣ አዲስ አበባ የከተማ ልማት ከባህላዊ ጥበቃ ጋር እንዴት ሊጣጣም እንደሚችል ከሀገር ባለፈ እንደ አህጉርም ተምሳሌት ያደርጋታል ብለዋል።

በርካታ ሀገራት ጎዳናዎችን፣ አደባባዮችን እና መናፈሻዎችን ወደ ደማቅ የበዓል ማክበሪያ ማዕከልነት በመቀየር ባህሎቻቸውን እያሳደጉ እና እያበለጸጉ ነው፤ ይላል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) The Impact of Heritage Conservation on Cultural Development በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ መስከረም 26 2025 ይፋ ያደረገው መረጃ፡፡

ለአብነትም ጃፓን፣ ስፔን እና ዩናይትድ ስቴትስ - ህዝባዊ በዓላቶቻቸው ከፍ ብለው እና ደምቀው እንዲታዩ ጎዳናዎቻቸውን እና አደባባዮቻቸውን በማስዋብ ዓለም አቀፍ ትኩረትን መሳብ ችለዋል፡፡

ጃፓን፣ ቶኪዮን በመሳሰሉ ከተሞቿ በየዓመቱ የሚከበሩት የአደባባይ በአላቶቿ በሰፋፊ አደባባዮች፣ መንገዶችና ፓርኮች ላይ የበዓሉ ታዳሚዎች በአበቦች፣ በዛፎች እና በውብ ፏፏቴዎች ደስ ብሏቸው እንዲያሳልፉ ታደርጋለች። ይህም በመላው ዓለም በዓላቱ ትኩረት እንዲስቡ ምክንያት እንደሆነም በመረጃው ተመላክቷል፡፡

በዓለም ዙሪያ የባህል እና የፈጠራ ኢንዱስትሪዎች በየዓመቱ ከ2 ነጥብ 25 ትሪሊዮን ዶላር በላይ ያመነጫሉ፤ ይህም ወደ 30 ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች የስራ ዕድልም ይፈጥራል፡፡ እንደ መረጃው ከሆነ የባህል ቱሪዝም ከዓለም ጉዞዎች ውስጥ 40 በመቶውን ይሸፍናል፡፡ በመሆኑም የኮሪደር ልማቱ የፈጠረው ውብና ምቹ ገፅታ በየዓመቱ ለሚከናወኑ ኃይማኖታዊ እና ህዝባዊ በአላት አይረሴ ትዝታን እና ተናፋቂ ድባብን ከመፍጠራቸው ባሻገር ከተማዋ በባህል ቱሪዝም ዘርፍም የበለጠ ተጠቃሚ የምትሆንበትን ዕድልም የሚፈጥር ነው፡፡

# ከነዳጅ ጥገኝነት ለመላቀቅ ምን ተሰርቷል?

**በስንታየሁ ምትኩ**

በመካከለኛው ምስራቅ ባለው ጦርነት ምክንያት በዓለም አቀፍ ደረጃ የነዳጅ አቅርቦት ሰንሰለት ላይ መስተጓጎል ተከስቷል፡፡ የዓለም የነዳጅ ዋጋ ከጦርነቱ በፊት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። በዚህም ምክንያት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው በእጅጉ እየተፈተነ ይገኛል። ሀገራት ችግሩን ለመቋቋም አዳዲስ የነዳጅ አቅርቦት አማራጮችን ከመፈለግ ባሻገር፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በስፋት የመጠቀምና የተለያዩ የቁጠባ ዘዴዎችን የመዘርጋት ሥራ እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡

ኢትዮጵያም በዚህ ረገድ የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደች ትገኛለች። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሰሞኑን ባስተላለፉት መልዕክት፡- “በመካከለኛው ምሥራቅ በተፈጠረው ቀውስ የተነሣ ነዳጅ ገዝተው የሚጠቀሙ ሀገሮች እንደልብ ለማግኘት ተቸግረዋል። በመሆኑም ችግሩ ተፈትቶ ወደ መደበኛው የነዳጅ አቅርቦት ሥርዓት እስክንመለስ ድረስ ነዳጅን በቁጠባና ለመሠረታዊ ነገሮች ቅድሚያ በመስጠት መጠቀም ይኖርብናል” ሲሉ ሁሉም አካላት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤም በተመሳሳይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያጋጠመው የነዳጅ አቅርቦት ችግር እስኪፈታ ድረስ ነዳጅን በቁጠባ መጠቀም እንደሚገባ ገልጸው፤ ለዚህም ነዋሪዎች አጫጭር መንገዶችን በእግር በመጓዝ፣ እንዲሁም የብስክሌት አማራጮችን እና የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በመጠቀም ትብብር እንዲያደርጉ የጠቅላይ ሚኒስትሩን መልዕክት የሚያጠናክር ጥሪ አቅርበዋል።

ኢትዮጵያ ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት፣ ብክለትን ለመቀነስ እና ሀገሪቱ ነዳጅ ከውጭ ለማስገባት የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ መጠን ለመቀነስ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኢንቨስትመንትን እና አስመጪዎችን ማበረታታትን ጨምሮ፣ ሕዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ የፖሊሲ አቅጣጫ መከተል ከጀመረች ዋል አደር ብላለች፡፡

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ በርኦ ሀሰን ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ሰፊ የዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። ከዚህ ባለፈ ነባርና ዕድሜ ጠገብ የሆኑ የነዳጅ ተሽከርካሪዎችን ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የመቀየር ሥራም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መኪናዎች ቁጥር ከ100 ሺህ በላይ መሆኑን የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ከአንድ ዓመት በፊት ለመገናኛ ብዙኃን ይፋ ያደረገው መረጃ ያሳያል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማም የትራንስፖርት ዘርፉን




ፎቶ- ከገጸ ድር

ቴዎድሮስ አደባባይ በሚገኘው ሜጋ አንፊ ቴአትር የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ሀይል ሲሞላ

ከነዳጅ ጥገኝነት ለማላቀቅ ከ100 በላይ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ አውቶብሶች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ እንደ ባሕር ዳር፣ አዳማና ጎንደር ባሉ የክልል ከተሞችም በኤሌክትሪክ የሚሠሩ አውቶብሶች ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ተደርገዋል፡፡ በኤሌክትሪክ ለሚሰሩ ተሽከርካሪዎች የሚሆኑ የኤሌክትሪክ ቻርጅ ማድረጊያ መሠረተ ልማቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ኢትዮ ቴሌኮም፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የግሉ ዘርፍ በስፋት እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በኮሪደር ልማት የተሽከርካሪዎች፣ የእግረኞችና የብስክሌት መንገዶችን በመገንባትና በማስፋት ነዋሪዎች ሞተር አልባ የብዝኃ ትራንስፖርት አማራጮችን እንዲጠቀሙ ማድረግን ጨምሮ የተለያዩ ሥራዎች በስፋት እየተከናወኑ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን ከማጠናቀቅ በተጨማሪ የነፋስ፣ የፀሐይና የጂኦተርማል ታዳሽ የኃይል ምንጮችን በማስፋፋት ከነዳጅ ጥገኝነት ለመውጣት መሠረት እየጣለች ትገኛለች። መንግሥት የወሰዳቸው እርምጃዎችና ነዳጅን በቁጠባ የመጠቀም ባህልን ማዳበር እንደ ሀገር ዘለቄታዊ የኢኮኖሚ ጥቅም የሚያመጡ እንደሆነ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ተመራማሪ ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡ በዓለም ላይ የነዳጅ አምራችና ላኪዎች ማኅበር (ኦፔክ) የነዳጅ አቅርቦትና ዋጋን ከፍና ዝቅ በማድረግ የሚወስኑበትንና ጫና የሚፈጥሩበትን ሁኔታ ለመቀነስ ሀገራት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በስፋት ወደ መጠቀም ገብተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ያጋጠመው የነዳጅ አቅርቦት ሰንሰለት መቆራረጥና የዋጋ መጨመር ሲታይ፣ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ማስፋፋት ላይ መስራት አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን ያሳያል፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላለች የኃይል ፍላጎቷን በታዳሽ የኃይል ምንጮች ላይ በመመስረት ለምታሟላ ሀገር በኤሌክትሪክ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን ማስፋፋት በጣም አዋጪ መንገድ ነው ብለዋል፡፡

መንግሥት በኤሌክትሪክ የሚሠሩ መኪናዎችን ለማበረታታት ባደረገው ጥረት አሁን ላይ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል መኪኖች በብዛት ሲንቀሳቀሱ እየታየ ነው፡፡ ይህ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ኢትዮጵያ በነዳጅ ላይ ያላትን ጥገኝነት አቃልሏል፡፡ ይህንን አጠናክሮ በመቀጠል ከነዳጅ ጥገኝነት እንድትወጣ መሥራት እንደሚገባ የምጣኔ ሀብት ተመራማሪው ሞላ (ዶ/ር) ይናገራሉ፡፡

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ከሰሞኑ “የኢትዮጵያን የትራንስፖርት ዘርፍ ወደ ኤሌክትሪክና የተፈጥሮ ጋዝ የማሸጋገር እና የነዳጅ ቁጠባ ሀገራዊ ጥሪ” በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ እንዳብራራው፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተፈጠረውን የነዳጅ ቀውስ ለመሻገር መንግሥት አስቀድሞ ከነዳጅ ጥገኝነት የሚያላቅቁና ዘላቂ ሀገራዊ ጥቅምን የሚያመጡ አዳዲስ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መሪነት ኢትዮጵያን ከውጭ ጥገኝነት ለማላቀቅና የራሷን የተፈጥሮ ጸጋ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ስትራቴጂካዊ እርምጃዎች ሲወሰዱ ቆይተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በመካከለኛው ምሥራቅ በተከሰተው ጦርነት ምክንያት የዓለም የነዳጅ ገበያ ለከፍተኛ አደጋ መጋለጡ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአራት ዓመታት በፊት የነዳጅና የሌላ ማበረታቻ እንዲያገኙ ያደረጉት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ፖሊሲ ዛሬ ላይ ሀገርን ከፈተና የሚታደግ ብልህ እና አርቆ አሳቢ ውሳኔ መሆኑን በተግባር አረጋግጧል፡፡

ሚኒስቴሩ ወቅታዊውን ዓለም አቀፍ ጫና ለመቋቋም እና የሀገርን ኢኮኖሚ በዘላቂነት ለመታደግ በሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ በመንግሥት እና በግል ተቋማት ዘንድ ተግባራዊ እንዲሆኑ ጥሪ ቀርቧል፡፡

የኤሌክትሪክ መኪናዎችን መጠቀምን እንደ ሀገራዊ ባህል ማዳበር፣ በነዳጅ እና በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ነዳጅን በመተው የኤሌክትሪክ ኃይልን ብቻ እንዲጠቀሙ ማስቻል፣ በነዳጅ የሚሠሩትን ወደ ኤሌክትሪክ እና ተፈጥሮ ጋዝ የመቀየር ሥራን ማጠናከር፣ እንዲሁም እስከ 20 ቶን የሚይዙ የጭነት ተሽከርካሪዎች ወደ ኤሌክትሪክ፤ ከ20 ቶን በላይ የሆኑት ደግሞ ወደ ተፈጥሮ ጋዝ እና ኤሌክትሪክ እንዲቀየሩ መንግሥት እና የግል ዘርፍ በቅንጅት እንዲሠሩ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል፡፡

ባቡሮችን፣ አውቶብሶችን እና ሌሎች የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቶችን በስፋት እና በአግባቡ መጠቀም፤ አገልግሎቱም በወጣለት ታሪፍ እና መርሐ-ግብር ያለ መቆራረጥ እንዲሰጥ በትብብር መሥራት እንዲሁም ከተሽከርካሪ አጠቃቀምና አነዳድ ባህል ለውጥ ጋር በተያያዘ ከአንድ ቤት ውስጥ ብዙ መኪናዎችን ይዞ መንገድ ከመውጣት ይልቅ በጋራ የመጠቀም ልምድን ማዳበርና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ፤ ይህም የውጭ ምንዛሬ ለማዳን፣ የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስና ዜጎች በዓለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ መዋዠቅ እንዳይጎዱ ለማድረግ እንደሚያስችል ሚኒስቴሩ ጠቁሟል፡፡

መንግሥት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በማስፋፋት የወሰደው እርምጃ በአሁኑ ወቅት ላጋጠመው ቀውስ ምላሽ በመሆን ቀላል የማይባል እፎይታ እንደሚሰጥ ያነሱት የምጣኔ ሀብት ተመራማሪው ሞላ (ዶ/ር)፤ ከዚህ ባሻገር ሙሉ በሙሉ ከነዳጅ ጥገኝነት የመውጣቱ ሂደት ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ አሁን ያጋጠመውን የነዳጅ አቅርቦት ችግርና ጫና ለመቀነስ ነዳጅን በቁጠባና አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ ብቻ መጠቀም ይገባል ብለዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንዳሉት፣ አሁን ያጋጠመውን ችግር ለመሻገር ተሽከርካሪዎችን አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች እና የሕዝብ ትራንስፖርት አማራጮችን መጠቀም ይገባል፡፡ ዜጎች በእግር እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ፣ ሳይክልና የተለያዩ ሞተር አልባ ትራንስፖርቶችን እንዲጠቀሙ የሚደረገው ጥረትም ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት አክለው ገልጸዋል፡፡

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሺዴ ሰሞኑን በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፣ ኢትዮጵያ ለነዳጅ ግዥ በየዓመቱ ከ4 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር በላይ ታወጣለች። መንግሥት በመቶ ቢሊዮን ብር በጀት ድጎማ እያደረገ ለኅብረተሰቡ እያቀረበ ይገኛል፡፡ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪና ድጎማ የሚቀርበው ምርት በገበያ ላይ ከተቀመጠው በላይ በከፍተኛ ዋጋ እየተሸጠ በመሆኑ፣ በሕገ-ወጥ ተግባር ላይ እየተሳተፉ የሚገኙ የመንግሥትና የተለያዩ አካላትን በሕግ ቁጥጥር ሥር በማዋል ተጠያቂ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል፡፡ ከዚህ ባሻገር የነዳጅ አቅርቦት አስተማማኝ እንዲሆንም መንግሥት አጣዳፊ ግዥዎች እየፈጸመና ከዲፖዎችም እያቀረበ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ ያለውን የነዳጅ ሀብት በከፍተኛ ቁጠባና ኃላፊነት መጠቀም ይገባል፡፡

# የኢድ አልፈጥር የበጎነት እሴት

**“በበዓላት የሚደረገው የመደጋገፍ እሴት በእለት ተእለት ህይወትም ሊተገበር ይገባዋል”**

**በለምለም አምባ መስጂድ ዋና ኢማም ሼህ አሊ መኮንን**



ፎቶ- ከፋይል

በለምለም አምባ መስጂድ ዋና ኢማም ሼህ አሊ መኮንን



ፎቶ- ከገፀ ድር

ድጋፍ የሚሹ ወገኖችን በገንዘብና ጉልበት ማገዝን ባህል ማድረግ ያስፈልጋል

**በስንታየሁ ምትኩ**

ወጣት ጀዋር ሱልጣን በአዲስ አበባ ቤተል እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ነው፡፡ በቤተል ተቅዋ መስጂድ የወጣት ማህበር ኃላፊ ነው፡፡ “ኢድ አልፈጥር በጉጉት የሚናፈቅና የሚጠበቅ የደስታ በዓል ነው፡፡ በዓሉን በሶላት፣ ከቤተሰብ፣ ወዳጅ ዘመድ፣ ከሰፈር ነዋሪዎች ጋር በመጠያየቅና አብሮ በመብላት እንዲሁም በደስታ ነው የማሳልፈው፡፡ ከዚህ ባሻገር በጎረቤትና በሰፈር የሚኖሩና በኑሮ አቅም የሚያንሳቸው ወገኖች፣ በዓሉን በደስታ እንዲያሳልፉ ከአካባቢው ወጣቶች ጋር በመሆን በተለያዩ መልኩ ድጋፍ እናደርጋለን” ሲል ተናግሯል፡፡

በእስልምና ማንኛውም ሰው በቤተሰቡ ቁጥር ልክ ዘካ ማውጣት ወይም መክፈል ይጠበቅበታል፡፡ ይህም አቅም ለሌላቸው ወገኖች የሚሰጥና በዓልን በደስታ እንዲያሳልፉ ለማስቻል ታስቦ የሚደረግ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ወጣት ጀዋር እንደሚገለፀው፣ እንደ ተቅዋ መስጂድ አማኙ ዘካ የሚያዋጣ ሲሆን የተሰበሰበውን አቅም ለሚያንሳቸው ሰዎች በአግባቡ እንዲዳረስ የማስተባበር ስራ ይሰራል፡፡ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ የሚወጣውን ዘካ በገንዘብ ተቀብሎ እህል (ዱቄት) ከገበያ በመግዛት ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች እንዲዳረስ ያደርጋሉ፡፡

ወጣት ጀዋር በእንደዚህ ዓይነት በጎ ስራ ከአስር ዓመት በላይ ሲሳተፍ መቆየቱንና ይህን በማድረጉም እርካታና ደስታ እንደሚሰማው ይናገራል፡፡ መደጋገፍ፣ መተሳሰብ፣ መተዛዘን፣ መተባበር፣ በጋራ መሆን በእስልምና ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና የሚበረታታ እሴት ነው። በኢድ አልፈጥር የሚከናወነው የዘካ ስርዓትም ቀጣዩ ትውልድም የመዋደድ፣ የመደጋገፍና የመተባበር እሴትን እንዲማር ያደርጋል፡፡ ምቀኝነት ያጠፋል፤ በማህበረሰብ መካከል ሰላምን ያመጣል ሲል የዘካን ፋይዳ ያብራራል፡፡

ሌላው የአካባቢው ነዋሪ ወጣት ዑስማን አብዱ ኢድ አልፈጥርን ጨምሮ በበዓላት ሁሉም ሰው በዓሉን በደስታ እንዲያሳልፍ ዘካ ከማውጣት ጀምሮ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች በማሰራጨት እንደሚሳተፍ ይናገራል፡፡ በሚኖርበት አካባቢ የሚገኘው የቤተል ተቅዋ መስጂድ የሚታወቅና በርካታ ቁጥር ያላቸው የእምነቱ ተከታዮች የሚሰግዱበት እንደመሆኑ፣ ከአማኙ ዘካ በመሰብሰብና ዱቄት በመግዛት ድጋፍ ለሚፈልጉ በሺህዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች ያሰራጫሉ፡፡ ይህም በየዓመቱ ኢድ አልፈጥር በመጣ ቁጥር በአደባባይ የሚከናወን እንደሆነ ይናገራል፡፡

ወጣት ዑስማን እንደገለፀልን፣ በረመዳን ወር በየቀኑ በቤተል አደባባይ ማታ ላይ በአፍጥር ሰዓት ለምስኪኖች (አቅመ ደካሞች) ምግብ በማቅረብ እንዲያፈጥሩ ይደረጋል፡፡ በማህበራዊ ሚዲያም የተቸገሩ ወገኖች ድጋፍ እንዲያገኙ ሀብት በማሰባሰብና በማዳረስ አግማስ ኢትዮጵያ እና ባቡል ኸይር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመሆን ተሳትፎ አድርጓል፡፡

“የተፈጠርኩት ለአላህ ለመገዛት ነው። ለአምላክ የምገዛበት አንደኛው መንገድ ለተቸገሩ ሰዎች መድረስና መኖር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በኪሴ ገንዘብ ካለ በገንዘብ፣ ከሌለ ደግሞ በጉልበትና በእውቀት ሰዎችን መደገፍ ያስደስተኛል፡፡” ሲልም በበጎነት ስራዎች ላይ ለምን እንደሚሳተፍ ይገልጻል፡፡

“ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ፤ ለሃምሳ ሰው ጌጡ” እንደሚባለው በቤተሰብ፣ በሰፈርና በአካባቢ ብሎም እንደሀገር የሚታዩትን ማህበራዊ ችግሮች እንደ ህዝብ ብንጋራቸው ቀላል ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ሁሉም ከራሱ ባሻገር ለሌላ ሰው መድረስ ይኖርበታል፡፡ በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በእውቀት፣ በጉልበትና በሀሳብ ለሰዎች ጥሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም አብሮ ለማደግ፣ እንደሀገር ችግሮችን ለማቃለልና ወደ ፈጣሪ ለመቅረብ የሚጠቅም ባህል ልናደርገው እንደሚገባ ወጣት ዑስማን ይናገራል፡፡

የረመዳንን ወር የእስልምና እምነት ተከታዮች በጾምና ሰላት፣ በምስጋናና በልግስና ያሳልፋሉ፡፡ በጾም መጨረሻ እና በሸዋል ወር የመጀመሪያ ቀን ላይ የኢድ-አልፈጥር በዓል በታላቅ ድምቀት ይከበራል፡፡ የኢድ በዓል በህዝበ ሙስሊሙ ዘንድ በጋራ በመስገድ እና የአላህን ስም በማውሳት (በተክቢራ) ይከበራል። በቤት ውስጥ፣ በሰፈር ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት ከወዳጅ ዘመድ ጋር በመሆን በሃላል ምግብና መጠጥ በአንድነትና በጋራ በደስታ ይከበራል፡፡

በኢድ በዓል ከሚከናወኑ ስነ ስርዓቶች መካከል ለአቅመ ደካሞችና ድኻዎች መለገስ (ዘካ) አንዱ ነው፡፡ ሼህ አሊ መኮንን በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የሚገኘው ለምለም አምባ መስጂድ ዋና ኢማም ናቸው፡፡ ዘካ ከእስልምና እምነት አምስት መሰረቶች መካከል መስጠት አንዱና ሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

ዘካ ሁለት ዓይነት መልክ አለው፡፡ በኢድ አልፈጥር ዋዜማ እና እለት የሚሰጥ የማፍጠሪያ ስጦታ “ዘካቱል ፊጥር” ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ማንኛውም ጿሚ የሆነ የእስልምና እምነት

ተከታይ ሊተገብረው የሚገባ ስርዓት እንደሆነ ሼህ አሊ ያስረዳሉ። “ዘካቱልማል” ሁለተኛው የዘካ ዓይነት ሲሆን በገንዘብ መልክ የሚወጣ ነው። አንድ ሰው ያለው ገንዘብ ፍላጎቱን ከማሟላት ባሻገር ተቀማጭ ከሆነና ተቀማጩ ገንዘብ ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ ከሆነ ባለገንዘቡ ዘካ የማውጣት ግዴታ አለበት፡፡ ይህም ባለሀብቶችን የሚመለከት ሲሆን በማንኛውም ጊዜ የሚከናወን ነው፡፡ አብዛኛው ሙስሊሞች የረመዳን ፆም ወቅቱን ጠብቀው ያወጣሉ። በጾም ወቅት የሚሰጥ ዛካ የሚያስገኘው ምንዳ (አጅር) እጥፍ ድርብ ነው፡፡

የረመዳን ጾም ሲፈታ የሚከናወነው ዘካቱል ፊጥር (የሚሰጠው ምጽዋት) ማንኛውንም ሙስሊም ገና የተወለደ ህጻን ልጅ፣ በኑሮ አቅመ ደካማ የሆነ፣ ትንሽ ወይም ትልቅ ሳይባል ሁሉም ሰው ሳይቀር በራሱና በቤተሰቡ ቁጥር ዘካቱል ፊጥር ማውጣት ይጠበቅበታል፡፡ ችግረኛ ሆኖ ዘካቱል ፊጥር ያወጣ ሰው፤ ከሌላ ሰው ዘካ መቀበል ይችላል፡፡

አንድ ሰው 2 ኪሎ ግራም ተኩል ዋጋ ያለው እህል (ስንዴ፣ በቆሎ፣ ቴምር፣ ገብስ ወይም ሌላ) መግዛት የሚችል ገንዘብ ማውጣት ይጠበቅበታል፡፡ ዘካ መስጠት የእስልምና መሰረት በመሆኑ ዘካ አለማውጣት ከእስልምና መሰረት እንደመውጣት እንደሚቆጠር ሼህ አሊ ያስረዳሉ፡፡

ዘካ መቀበል ያለባቸው ወይም የሚሰጣቸው ድኻዎች፣ በአካል ጉዳት፣ በህመምና በተለያየ ምክንያት ሰርተው መብላት የማይችሉ (ምስኪኖች)፣ ከሌላ እምነት ወደ እስልምና የገባና ችግር ያለበት፣ ዕዳ ኖሮበት እዳውን መክፈል ላልቻለ (በማጣት) እና ሌሎችን ያካትታል፡፡

ሼህ አሊ እንደሚያስረዱት፣ የዘካ ዓላማ በቅርብ የሚደግፋቸው የሌላቸውና ድሃዎች በአቅም ማነስ ምክንያት ቤታቸውን ዘግተው እንዳይውሉ፣ እንዳይተክዙ፣ ገንዘብ ማጣት እንደ ነውር ተደርጎ እንዳይታይ፣ በማጣታቸው እንዳይሰበሩ የሚጠግን፣ የህብረተሰቡ አንድ ወገን መሆናቸውን ለማሳየት የሚሰጥ ምጽዋት ነው። ለችግረኞችና ድሃዎች ዘካ መስጠት በፈጣሪ (አላህ) ዘንድ ደስታ ይፈጥራል። ከሞት በኋላ ባለው ህይወትም ድሃን በመርዳት ግዴታውን የተወጣ ጥሩ ቦታ ይጠብቀዋል፡፡

በኢድ አልፈጥር ወቅት ልጆች አዲስ ልብስ እንዲገዛላቸው ይፈልጋሉ፡፡ አቅም የሌላቸው ለልጃቸው ልብስ፤ መማሪያ ደብተርና እስክርቢቶ መግዛትና ሌሎች የሚያስፈልጋቸውን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት ይቸገራሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ሀብት ያለው ችግረኛው ሳይናገር በህሊና ተረድቶ፣ ‘የማን ልጆች ናቸው በማጣት ቀልባቸው የተሰበረው’ በማለት በቶሎ መድረስ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ማድረግ ነገ በተጨነቁ ሰዓት አላህ እንዲደርስላቸው ያደርጋል፡፡ በአዲስ አበባ በዘካ በሚሰጣቸው ገንዘብ ልጆቻቸውን ልብስ የሚያለብሱ ብዙ ሰዎች እንዳሉ ሼህ አሊ ያነሳሉ፡፡

ሼህ አሊ እንዳሉት፣ በእስልምና ዘካ ድሆች በማጣታቸው የማይተክዙበት፣ ሀብታሞች በማግኘታቸው የማይኮፈሱበት፣ በሀብታሞች ንብረት ላይ የድሀዎች ሀብት ያለበት መሆኑን የሚያስተምር ጥሩ የሆነ የመረዳዳት ልምድ ነው፡፡ በአዲስ አበባ የእስልምና እምነት ተከታዮች የዘካ ግዴታቸውን በስፋት የሚወጡ ሲሆን ይህም ማህበራዊ ችግሮችን በማቃለል፣ መደጋገፍ፣ መተሳሰብን በማስረፅ፣ ፍቅርን፣ መግባባትን በማጠናከር ከፍተኛ ፋይዳ እየተጫወተ ይገኛል፡፡

ሼህ አሊ እንደገለጹት፣ በአዲስ አበባ ወጣቶች በበጎ ፈቃደኝነት በመሳተፍ ችግረኞች በዓልን በደስታ እንዲያሳልፉ ሀብት በማሰባሰብና የተሰባሰበውን በማሰራጨት ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ። በለምለም አምባ መስጂድ የሚገለገሉ

ወደ ገጽ 16 ዞሯል

## ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የምርጫ ምንነት፣ መርሆች እና ዓይነቶች

## ክፍል ሁለት

ናደው ወርቁ (ዐቃቤ ህግ)

ውድ አንባቢዎቻችን፤ ባለፈው ዕትማችን በዋና ርዕሰ ጉዳይ መነሻነት የምርጫ ምንነት ፤ የምርጫ መርሆዎች እና የምርጫ አይነቶች እና ተያያዥ ጉዳዮችን አስነብበናችኋል። ክፍል ሁለትን ደግሞ እንደሚከተለው አዘጋጅተንላችኋል። መልካም ንባብ!

### የምርጫ አፈጻጸም የመራጮች ምዝገባ

አንድን ምርጫ ለማካሄድ በቅድሚያ የሚመርጠው አካል መታወቅና መመዝገብ አለበት፡፡ በዚህ መሠረት የመራጮችን ምዝገባ በተመለከተ አንድ ሰው በመራጭነት ለመመዝገብ ማሟላት ስለሚጠበቅበት መስፈርት እንዲሁም የት እና መቼ መመዝገብ እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 18 መሰረት አንድ መራጭ በመራጭነት ለመመዝገብ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

- ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆን፤
- በምርጫ ክልሉ ቢያንስ 6 ወር መኖር፤
- ድምጽ በሚሰጥበት ዕለት እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡ ይሄን ጉዳይ በሚመለከት አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 18(1)(ለ) በምዝገባው ዕለት እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ መሆን እንደሚጠበቅበት ያስቀምጣል። ይሁን እንጂ በዚህ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1394/2017 አንቀጽ 2(5) መሠረት ድምጽ በሚሰጥበት ዕለት እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሚሆን ከሆነ በምዝገባው ዕለት 18 ዓመት ባይሞላውም በመራጭነት መመዝገብ ይችላል፡፡

በመርህ ደረጃ ከላይ የተዘረዘሩትን ሶስት መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ዜጋ በመራጭነት መመዝገብ ይችላል፡፡ ነገር ግን በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 18(3) መሠረት በልዩ ሁኔታ የሚከተሉት ሰዎች በመራጭነት መመዝገብ አይችሉም፡፡

- በአዕምሮ ህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው መሆኑ ስልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት ሰው፤
- የመምረጥ መብቱ በህግ ወይም አግባብ ባለው ህግ መሠረት በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገደበበት ሰው፡፡



### የመራጮችን የምዝገባ ጊዜ በተመለከተ

በአዋጅ አንቀጽ 19 መሰረት የጠቅላላ ምርጫ መራጮች ምዝገባ ምርጫ ቦርድ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚጀመር እና የሚጠናቀቅ ሲሆን ምዝገባው ከመጀመሩ ከ15 ቀን በፊት ጀምሮ በተከታታይ በመገናኛ ብዙሃንና በማስታወቂያዎች አማካኝነት ለህዝቡ ይገልጻል፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ የሆነ ጉዳይ ካጋጠመ ቦርዱ ልዩ የምዝገባ ጊዜ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በመራጮች የምዝገባ ጊዜ መመዝገብ ያልቻለ ሰው ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ በልዩ ሁኔታ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 20 መሰረት መራጮችን መመዝገብ የሚቻለው በምርጫ ጣቢያ ብቻ ነው። በመርህ ደረጃ ከምርጫ ጣቢያ ውጭ ቤት ለቤት እየተዘዋወሩ ወይም በመንገድ ላይ መራጮችን መመዝገብ የተከለከለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በልዩ ሁኔታ በአርብቶ አደሮች አካባቢ ተንቀሳቃሽ የምዝገባ ጣቢያ በማቋቋም ወይም ቤት ለቤት በመዘዋወር ምዝገባ ማካሄድ ይቻላል። እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የራሱ የመራጮች መዝገብ ይኖረዋል፡፡ በአካል ምርጫ ጣቢያ ሄዶ ከመመዝገብ ባሻገር ምርጫ ቦርድ በሚያዘጋጀው የቴክኖሎጂ አማራጭ መመዝገብ እንደሚቻል አዋጅ ቁጥር 1394/2017 አንቀጽ 2(6) ያስቀምጣል፡፡

የመራጮች አመዘጋገብ ስርዓትን በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 21 በዝርዝር የሚያስቀምጥ ሲሆን፤ አንድ መራጭ በመርህ ደረጃ የሚመዘገበው በሚኖርበት አካባቢ ባለ የምርጫ ጣቢያ ሲሆን ለመመዝገብ ማንነቱን የሚገልጽ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ሊኖረው ይገባል። በዚህ አዋጅ መሰረት ፓስፖርት እና የቀበሌ መታወቂያ በአማራጭነት የተቀመጡ ናቸው፡፡ ሆኖም መታወቂያው ወይም ፓስፖርቱ አለመታደሱ ከምዝገባ አያግድም፡፡

ይሁን እንጅ ተመዝጋቢው የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት የሌለው ከሆነ በቅርቡ ፎቶ ግራፍ ተደርጎበት የተሰጠ መንጃ ፈቃድ፣ የመኖሪያ የምስክር ወረቀት፣ ከውትድርና የተገለለበት ሰነድ፣ የትምህርት ቤት መታወቂያ እና ሌሎች መሰል የማንነት መለያ ሰነዶችን ማቅረብ ከቻለ መመዝገብ ይችላል፡፡

ማንነቱን የሚገልጽ ምንም ዓይነት ሰነድ ማቅረብ ያልቻለ ሰው የምርጫ ጣቢያው በተቋቋመበት ቀበሌ ለረጅም ጊዜ መኖሩ በሶስት ምስክሮች ከተረጋገጠ ለመራጭነት መመዝገብ ይችላል፡፡ ህጉ መራጮችን ለመመዝገብ ሰፋ ያለ ማእቀፍ አዘጋጅቷል ለማለት ይቻላል፡፡

አንድ መራጭ ሲመዘገብ ሙሉ ስሙ ከእነ አያቱ፣ የሚኖርበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የምርጫ ጣቢያ፣ የቤት ቁጥር፣ መንደር ወይም ጎጥ፣ የመዝገብ ቁጥር፣ የምዝገባ ተራ ቁጥር፣ የመዝገብ ገጽ፣ የመራጩ ፊርማ፣ የመዝጋቢው ፊርማ እንዲሁም የተመዘገበበት ቀን ተሞልቶ ለመራጩ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ይሠጠዋል፡፡ የመራጮች ምዝገባ ለማከናወን ከምርጫ አስፈጻሚዎች ቢያንስ ሶስቱ በጣቢያው መገኘት አለባቸው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 22 መሰረት የመራጮች መዝገብ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት። የምዝገባ ተራ ቁጥር፣ የምዝገባ ቀን፣ የተመዝጋቢው ሙሉ ስም ከእነ አያቱ፣ የትውልድ ቀን እና ዓመተ ምሕረት፣ ዕድሜ፣ ጾታ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ በምርጫ ክልሉ የኖረበት የጊዜ ቆይታ፣ የምዝገባው ዕለት ፊርማ (የጣት ወይም የጽህፈት)፣ የምርጫው ዕለት ፊርማ(የጣት ወይም የጽህፈት)፣ የቤት ቁጥር/መንደር/ጎጥ/ የቦታው ልዩ መጠሪያ፣ ልዩ አስተያየት እንዲሁም በልዩ ሁኔታ ለሚቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮቹ ልዩ ሁኔታዎች የሚመዘገቡበት ዓምድ መያዝ አለበት፡፡

ማንኛውም መራጭ በአንድ ምርጫ ጣቢያ ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ ወይም በሌላ የምርጫ ጣቢያ ድጋሜ መመዝገብ አይችልም፡፡ በዚህ መሰረት አንድ መራጭ አንድ የመራጭነት መታወቂያ ብቻ ይኖረዋል፡፡ የመራጭነት መታወቂያው የጠፋበት ወይም የተበላሸበት መራጭ ከድምጽ መስጫው ዕለት በፊት ከሆነ በማንኛውም የምርጫ ጣቢያው የስራ ሰዓት በድምጽ መስጫው ዕለት ከሆነ ደግሞ የምርጫው ሰዓት ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ጣቢያው ማመልከት ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት የምርጫ ጣቢያው ጽ/ቤት ከመራጮች መዝገብ ጋር በማመሳከር እና በቃለ ጉባኤ በመያዝ አዲስ የመራጭ መታወቂያ ሊሰጠው ወይም ድምጽ እንዲሰጥ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 25 መሰረት በመራጮች ምዝገባ መጨረሻ ቀን በመዝገቡ ላይ ከመጨረሻው ተመዝጋቢ ቀጥሎ ባለው ክፍት ቦታ የጣቢያው ምርጫ አስፈጻሚዎች ተፈራርመውበት መዝገቡ የሚዘጋ ሲሆን ምርጫ ቦርድ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር መዝገቡ ከተዘጋና ከተፈራሙበት በኋላ በመዝገቡ ላይ አዲስ መራጭ መመዝገብ ወይም ሌላ ጽሑፍ መጻፍ አይቻልም፡፡

የመራጮች ምዝገባ እንደተጠናቀቀ የመራጮች መዝገብ በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ለ10 ቀናት ይፋ በማውጣት ህዝብ በግልጽ እንዲያየው መደረግ አለበት፡፡ በጣቢያው የሚወዳደሩ ተመራጮች ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ጥያቄ በማቅረብ የመራጮች መዝገብን መመልከት ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ የመራጮች መዝገብ ለምርጫ ቦርድ የክልል ምርጫ ጽ/ቤት ወይም ለምርጫ ጣቢያው ቅርብ ለሆነ የምርጫ ጽ/ቤት መላክ አለበት፡፡

አንባቢዎቻችን ክፍል ሦስትን በሚቀጥለው ሳምንት ይዘን እንቀርባለን፡፡

ኢኮኖሚ

# በተግባራዊ ልምምድ የታነጹ እጆች

- **በሦስተኛው ዙር የስራ ላይ ልምምድ የተሳተፉ ወጣቶች መጋቢት 15 ቀን 2018 ዓ.ም ይመረቃሉ**

**በደረጀ ታደሰ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኘው የሥራና ክህሎት ቢሮ፣ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመተባበር እየተተገበረ ያለው "ብቃት" የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ያለሥራ የተቀመጡ ወጣቶችን የሥራ ባለቤትና የቤተሰብ ደጋፊ እያደረገ ይገኛል።

የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር፣ ለመዲናዋ ወጣቶች ሁነኛ የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ሆኖ ስለማገልገሉ ከዚህ ቀደም የተከናወኑ የመርሃ ግብሩ የሁለት ዙር ፍሬያማ ውጤቶች ምስክር ናቸው፡፡ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም ለጉዳዩ ተገቢ ሽፋን ሰጥቷል። በዚህም በሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር የታቀፉ ወጣቶች፡- ከሥራ አጥነት ተላቅቀው፣ የነበረባቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቦናዊ ጫና አስወግደው፣ ከጥገኝነት ራስን ወደ መቻል ተሸጋግረው፣ ተስፋ መቁረጥን በሥራ ስለት ቆርጠው፣ ዛሬን በጥረት ነገን በተሻለ ርዕይ ቀርፀው... ጉዞ ወደ ፊት የሚል ወኔን የተላበሱ የተግባር ሠዎች መሆናቸውን ከአንደበታቸው ሰምቷል፤ በሥራ ቦታቸው ተገኝቶ ተምልክቷል፤ በአሠሪ ድርጅቶች ምስክርነትም አረጋግጧል፡፡ በሦስተኛው ዙር ተሳታፊ የሆኑ ከስምንት ሺህ የሚልቁ ወጣቶችም፤ በተመሳሳይ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድና መልካም የሥራ ሥነ ምግባር የተላበሱ ትንታግ የሥራ ሰዎች ለመሆን የበቁበት ጊዜ ላይ ይገኛሉ፡፡

ወጣት ገነት ረጋሳ በጉለሌ ክፍለ ከተማ በሚገኝ የአልባሳት ማምረቻ ኢንዱስትሪ ውስጥ በቋሚነት ተቀጥራ የምትሠ ወጣት ናት። ገነት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተፈትና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግባት የሚያስችል ውጤት ባለማምጣቷ ምክንያት ተስፋ ቆርጣ በቤት ውስጥ ለመቀመጥ ተገድዳ ነበር። "በሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ከመታቀፌ በፊት ምንም ዓይነት ሙያም ሆነ ሥራ አልነበረኝም" የምትለው ገነት፣ ስለ መርሃ ግብሩ መረጃ እንደሰማች ወዲያውኑ መመዝገቧን ታስታውሳለች።

በመርሃ ግብሩ አማካኝነት የተለያዩ ስልጠናዎችን የወሰደችው ወጣት ገነት፣ በራሷ ምርጫ ወደ አልባሳት ኢንዱስትሪ ተቀላቀለች። በሦስት ወራት የሥራ ላይ ልምምድ ቆይታዋም ጨርቅ መቁረጥ፣ ኦቨርሉክ ማድረግ እና መስፋት የመሳሰሉ መሠረታዊ ሙያዎችን በሚገባ ተክናለች። "የሥራ ላይ ልምምድ እንዳጠናቀቅሁ ድርጅቱ በቋሚነት ቀጠረኝ፤ አሁን በወር 5 ሺህ 500 ብር ደመወዝ ይከፈለኛል" በማለት በኩራት ትናገራለች። ገነት አክላም አብዛኞቹ ወጣቶች በመንግስት ተቋማት መቀጠርን ብቻ እንደሚጠብቁና ይህ ሳይሳካ ሲቀር ተስፋ እንደሚቆርጡ ጠቁማ፣ በየአካባቢው ያሉ ዕድሎችን መጠቀም እንደሚገባ ትመክራለች። በቀጣይም ከምታገኘው ገቢ በመቆጠብ የግል ሥራዋን የመጀመር ትልቅ ህልም እንዳላት ገልፃለች።

በተመሳሳይ ወጣት ቤተልሔም ኪዳነማርያም፣ የ10ኛ ክፍል ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ለስድስት ወራት ያለ ሥራ በቤት ውስጥ መቀመጧ ለከፍተኛ ድብርትና ጭንቀት ዳርጓት እንደነበር ትገልጻለች። "እነዚያ ጊዜያት በጣም ረጅምና አሰልቺ ነበሩ" የምትለው ቤተልሔም፣ በሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብሩ አማካኝነት ወደምትወደው የአልባሳት ሙያ በመቀላቀሏ፣ ዕድሉ ከህልሟ ጋር ለመገናኘት እንደድልድይ እንደጠቀማት ትናገራለች። አሁን ላይ ስፌት የመስፋትና ፓተርን የማውጣት ሙያን ተክናለች፡፡ ከቤተሰብ ጥገኝነት ወጥታለች፡፡ ሙያዊ ክህሎቷን፣ ዕውቀቷንና የሥራ ሥነ ምግባሯን ከማሻሻሏ በተጨማሪ፣ ከድርጅቱ ባለቤቶች ያገኘችው ልምድ ለቀጣይ ህይወቷ ትልቅ መሠረት ሆኗታል።



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው መካከል ወጣት ቤተልሔም ኪዳነማርያም እና ወጣት ቤዛዊት ጥላሁን

> **መንግስት የመርሃ ግብሩን ውጤታማነት በማየት፣ በመንግስት ሙሉ ወጪ የሚከናወን 4ኛ ዙር የፓይለት ፕሮግራም በ115 ሚሊዮን ብር በጀት፣ በተመረጡ 20 ወረዳዎች፣ 3 ሺህ ወጣቶችን በመያዝ ተጀምሯል**

የመርሃ ግብሩ ተጠቃሚዎች በአልባሳት ዘርፍ ብቻ የተገደቡ አይደሉም። ከአውቶሞቲቭ ወይም ከተሽከርካሪ ጋር የተያያዘ ሙያን በሚጠይቁ እና ሌሎች ዘርፎች ላይ የተሠማሩም ብዙዎች ናቸው፡፡ ወጣት ቤዛዊት ጥላሁን ከእነዚህ መካከል አንዷ ናት፡፡ በትምህርት ዝግጅቷ በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ገብታ በኤሌክትሪክ ሙያ ብትሰለጥንም ያለሥራ በቤት ለመቀመጥ ተገድዳ ነበር። ገና ከጅምሩ በአውቶሞቲቭ ዘርፍ መሰማራትን ውስጣዊ ፍላጎቷ አድርጋ ቆይታለች፤ ለዚህም ይረዳት ዘንድ ተያያዥ ሙያን በኮሌጅ ገብታ ሰልጥናለች። ይሁን እንጂ ፍላጎቷ እንዲሰምር ትልቁን ድርሻ የተወጣው የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር መሆኑን አልሸሸገችም፡፡

"የሥራ ላይ ልምምድ እንዳደርግ በፍላጎቴ መሰረት የተመደብኩበት የኤክራም አውቶሞቲቭ ድርጅት መሆኑን ሳውቅ ህልሜ እውን መሆን እንደጀመረ ተረዳሁ፡፡ ምክንያቱም ድርጅቱ በከተማችን ካሉ ታዋቂ የአውቶሞቲቭ ተቋም አንዱ ነው፡፡ ወደ ድርጅቱ ለጥገና የሚመጡት አብዛኞቹ ተሽከርካሪዎች ዘመናዊና ከኤሌክትሪክ ጋር የተያያዘ ሥራ የሚጠይቁ በመሆናቸው አቅሜን በሚገባ አሳድጌያለሁ፡፡ በሥራ ላይ ካሉ ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎች ብዙ ነገሮችን ተምሬያለሁ፡፡" ትላለች። ዛሬ በ4 ሺህ ብር ደመወዝ ተቀጥራ የምትሠራው ቤዛዊት፣ ወጣቶች ሥራ ሳይመርጡና ሳይንቁ መጀመር እንዳለባቸው መልዕክቷን አስተላልፋለች።

በሌላ በኩል፣ ወጣት ዘውዴ መሃመድና አራት ጓደኞቿ በጋራ በመሆን የራሳቸውን የሴቶች ፀጉር ቤት ከፍተው ወደ ሥራ ገብተዋል። ቀደም ሲል ሥራ አጥና ክህሎት አልባ የነበሩት እነዚህ ወጣቶች፣ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሥራና ክህሎት ጽሕፈት ቤት እና ልምምድ ባደረጉበት ድርጅት ድጋፍ አማካኝነት ዛሬ የሥራ ባለቤት ሆነዋል። የክፍለ ከተማው አስተዳደር የአንድ ወር የቤት ኪራይ የከፈለላቸው ሲሆን፣ የልምምድ ድርጅቱ ደግሞ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችንና ግብዓቶችን አሟልቶላቸዋል። "ተቀጥረን ለመሥራት እናስብ የነበርን ወጣቶች የራሳችንን ሥራ መጀመር ችለናል" በማለትም የጅምራቸውን ስኬታማነት ገልጸዋል።

የዮኬት ማኑፋክቸሪንግ ድርጅት መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ቤዛዊት ነጌሶ፣ መርሃ ግብሩ ለድርጅታቸውም ትልቅ ጥቅም ማምጣቱን ይናገራሉ። ድርጅታቸው 30 ተለማማጅ ወጣቶችን በመቀበል በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ልምምድ እንዲያደርጉ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ወደ ድርጅቱ የገቡት ወጣቶች ሙሉ ለሙሉ ልምምዱን በሚገባ በማጠናቀቃቸው፣ ሙያዊ ክህሎትንና የሥራ ሥነ ምግባርን በመላበሳቸው ሁሉም በድርጅቱ በቋሚነት መቀጠር ችለዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከላይ ሃሳብና አስተያየታቸውን የሰጡት ወጣት ገነት ረጋሳ እና ወጣት ቤተልሔም ኪዳነማርያም እንደሚገኙበት ተናግረዋል፡፡

ሥራ አስኪያጇ፤ "ወጣቶቹ በሙያ ብቁና በሥራ ሥነ- ምግባር የታነጹ ናቸው፤ በመካከላችን በነበረው መልካም ግንኙነት በ15 ቀናት ውስጥ ወደ ማምረት ሥራ መግባት ችለዋል" ብለዋል። ይህ መርሃ ግብር ድርጅታቸው የሠራተኛ ኃይል ፍላጎቱን በሰለጠነ ሰው እንዲተካ እንደረዳውም ገልፀዋል።

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሥራና ክህሎት ጽሕፈት ቤት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ስፔሻሊስት አቶ ፍቅረስላሴ ንጉሴ እንደገለጹት፣ በክፍለ ከተማ አስተዳደሩ ስር በሦስተኛው ዙር ብቻ 1 ሺህ 113 ወጣቶች በተለያዩ 135 ድርጅቶች ውስጥ ልምምድ አድርገዋል። ከእነዚህም ውስጥ 60 ከመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። በእያንዳንዱ ዙር ከአንድ ሺህ በላይ ወጣቶችን በቋሚነት ወደ ሥራ ማሰማራት ተችሏል።

አቶ ፍቅረስላሴ አያይዘውም፤ "የሥራ ላይ ልምምድ ለሚያደርጉ ወጣቶች እንደተቋም የተለያዩ ድጋፎች ይደረግላቸዋል፡፡ ድጋፍና ክትትሉ በተቋሙ ብቻም ሳይሆን ከከፍተኛ አመራር ጀምሮ የተለያዩ ተቋማት እንዲሁም ሕዝቡ በቀጥታ የሚሳተፍበት ነው፡፡ የድርጅቶችና ኢንዱስትሪዎችም ሚና ከፍተኛ ነው" ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራና ክህሎት ቢሮ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ሰብህዲን ሱልጣን፣ የዓለም ባንክ ለዚህ ፕሮጀክት እያደረገ ያለውን የበጀት ድጋፍ በከፍተኛ ሁኔታ ያደንቃሉ። ይህ ፕሮጀክት ከ2014 እስከ 2018 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በአጠቃላይ 49 ሺህ ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ እየሠራ እንደሚገኝ በማስታወስ፤ "የዓለም ባንክ ፕሮጀክት የመጨረሻ ምዕራፍ በሆነው በሦስተኛው ዙር የተሳተፉ 8 ሺህ 852 ወጣቶች የስድስት ወራት ቆይታቸውን አጠናቅቀዋል፤ በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡ ይፋዊ የምረቃ ሥነ ስርዓቱም በከተማ አቀፍ ደረጃ የፊታችን ማክሰኞ፣ መጋቢት 15 ቀን 2018 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ስታዲየም ይከናወናል" ብለዋል።

በተጨማሪም፤ መንግስት የመርሃ ግብሩን ውጤታማነት በማየት፣ በመንግስት ሙሉ ወጪ የሚከናወን 4ኛ ዙር የፓይለት ፕሮግራም በ115 ሚሊዮን ብር በጀት፣ በተመረጡ 20 ወረዳዎች፣ 3 ሺህ ወጣቶችን በመያዝ መጀመሩን ገልጸዋል። ይህ ተግባር እንደ ከተማ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሥራ አጥነት ቁጥርን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ የሚያስችል ቁልፍ መሣሪያ መሆኑ ታምኖበታል።

የ"ብቃት" መርሃ ግብር ወጣቶች ሙያዊ ክህሎትና የሥራ ሥነ- ምግባር እንዲላበሱ በማድረግ ረገድ ትልቅ ለውጥ እያመጣ ይገኛል። ወጣቶቹም ከጥገኝነት ወጥተው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የሚረዱበት፣ አልፎም የራሳቸውን ሥራ የሚፈጥሩበት ዕድል ተመቻችቶላቸዋል። ስለሆነም፤ እንዲህ ዓይነቱን በቅንጅትና በትብብር ዕውን የሚሆን ፍሬያማ የተግባር እንቅስቃሴ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ ይገባል እንላለን፡፡

SIKET BANK

እንኳን ለ1447ኛ የዒድ አል-ፈጥር በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

በዓሉ የሰላም፣ የፍቅር እና የስኬት እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ።

ዒድ ሙባረክ!

ዳምጠው አለማየሁ
ዋና ሥራ አስፈፃሚ

8342 www.siketbank.com info@siketbank.com

ስኬት ባንክ የስኬትዎ መሰረት!

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉቤኤ
Addis Ababa City Administration Land Tenure Expropriation and Compensation Affairs Appellate Tribunal

የመሬት ሀብት የከበረና ውስን ሀብት በመሆኑ አጠቃቀሙ በጥንቃቄ ሊመራ ያስፈልጋል። በሀገራችን ኢትዮጵያ ስለ መሬት ባለቤትነትና ይዞታ ከፖሊሲም በላይ በሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌ የሚመራ መሠረታዊ ሀብት ነው። መንግስት ንብረቱን ወይም ንብረቱ የሚገኝበትን ቦታ ለሕዝብ ጥቅም የሚፈለግ ከሆነ፣ ንብረቱን ወይም ንብረቱ የሚገኝበትን ቦታ በእጁ ከማስገባቱ በፊት አስቀድሞ ለባለንብረቱ ካሳ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40(8) ስር ተደንግጓል።

የመሬት ማስለቀቅን አስመልክቶ ያሉ ዋና ዋና ሕጎች አዋጅ ቁጥር 1161/2011፣ አዋጅ ቁጥር 1336/2016፣ ደንብ ቁጥር 472/2012፣ መመሪያ ቁጥር 79/2014 እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተቋቋመበት ደንብ ቁጥር 30/1994 መጥቀስ ይቻላል።

ሁሉም የከተማችን፣ የሀገራችንና የውጪ ሀገራት የዲፕሎማሲ ማህበረሰብ ጭምር እንደሚመሰክሩት ዛሬ ላይ አዲስ አበባ ከተማ እንደገና እንደ አዲስ እየተገነባች ያለች ከተማ መሆኗ እሙን ነው። አሮጌ መንደሮች እየፈረሱ ረጃጅም ሕንፃዎች እየተገነቡ ነው። እነዚህ የሕንፃ ግንባታዎች፣ የልጆች መጫወቻ ቦታዎች፣ የእግረኛ መንገዶች፣ የሳይክል መንገዶች፣ በአጠቃላይ መዲናዋን ይመጥናሉ የተባሉ ማራኪ ዕይታ ያላቸው ኮሪደሮች እና ሌሎች ሲገነቡ የነዋሪውን ቤትና ንብረት መንካቱ አይቀሬ ነው። በዚሁ ለልማት ሲባል መንግስት የግለሰቦችን ይዞታ ማስለቀቅ ቢችልም ግን ደግሞ ላስለቀቀው ይዞታ ምትክ ቦታ እና ለፈረሰው ንብረት ተገቢውን ካሳ ይሰጣል።

ምትክ ቦታ እና ካሳን በተመለከተ የሕብረተሰቡን ቅሬታ ለመቀነስ የጉባኤውን ስልጣን ተደራሽነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ስለዚህ የከተማው ነዋሪዎች የዚህን ጉባዔ ራዕይ ለማሳካት ከተደራሽነቱ አንፃር እንዲሁም ቀልጣፋና ውጤታማ ውሳኔ እንዲሰጥ የበኩላችሁን አስተዋፅኦ እንድታደርጉ መልዕክቴን ለማስተላለፍ እወዳለሁ።

መልካም በዓል!

ስለ ጉባኤው ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት
በስልክ ቁጥር :- +251 115 511 580 ወይም Website:- www.ulc.gov.et ማግኘት ይቻላል።
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ

# የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ጥቁምታ


**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ሙዚቃ፣ የስዕል አውደ ርዕይ፣ የመጽሐፍት ምረቃ፣ የግጥም ምሽት እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጽሐፍት

የ“ፍቅር እስከ መቃብር” መጽሐፍ 60ኛ ዓመት በዛሬው እለት ይከበራል፡፡ በመርሃ ግብሩ ላይ ኤምሬትስ ፕሮፌሰር ሽብሩ ተድላ፣ ታዬ አሰፋ (ዶ/ር)፣ ሰዓሊ እሸቱ ጥሩነህ እና ደራሲ ህይወት እምሻውን ጨምሮ በርካታ ደራሲያንና ታዳሚያን እንደሚገኙ ተገልጿል፡፡ መጽሐፉ የታተመበትን 60ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው ይህ ፕሮግራም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ቀበና ካቶሊክ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ፣ ወደ ሳንፎርድ ትምህርት ቤት በሚወስደው መንገድ፣ ባማ አዲስ ሕንፃ አጠገብ፣ FSS አዳራሽ ይካሄዳል፡፡

በሌላ መረጃ “ፍቅር አይጻፍም” የተሰኘው መጽሐፍ ከነገ በስትያ ይመረቃል፡፡ የገጣሚ አቤል ያለውን ግጥምና ሽርፍራፊ ታሪኮችን የያዘው ይህ መጽሐፍ 4 ኪሎ በሚገኘው ዋልያ መጽሐፍት አዳራሽ ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ይመረቃል፡፡ በምርቃት ሥነ ስርዓቱ ላይም አንጋፋና ወጣት ደራሲያንና ገጣሚያን እንደሚታደሙ ተገልጿል፡፡













ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## የስዕል አውደ ርዕይ

ሴት ደራሲያን ስራዎቻቸውን ያቀረቡበት “የፈጠራ ጉዞን ማስተጋባት” የተሰኘው የስዕል አውደ ርዕይ በዕይታ ላይ ይገኛል፡፡ አውደ ርዕዩ ከሴት ሰዓሊያን ማህበር የ17 ሰዓሊያን ስራዎች የቀረበበት ነው፡፡ ፈንድቃ የባህል ማዕከል እና ሀያት ሪጀንሲ ሆቴል በመተባበር ያዘጋጁት ይህ አውደ ርዕይ 24 ሰዓት ለተመልካች ክፍት ሲሆን የፊታችን መጋቢት 21 ቀን 2018 ዓ.ም ይጠናቀቃል፡፡

በተጨማሪም የሚኪያስ አበራ የግል የሥዕል ኤግዚቢሽን በአርታዊ ጋለሪ በእይታ ላይ ይገኛል፡፡ “የመንደር ሹክሹክታ፡ ትዝታ እና ንብረት” (Village Whispers: Memory and Property) የተሰኘ ስያሜ የሰጠው ይህ አውደ ርዕይ የማህበረሰቡን አኗኗር፣ ታሪክ፣ ህይወት እና ተስፋ የሚያሳዩ ስራዎች የቀረቡበት ነው፡፡ አውደ ርዕዩ እስከ መጋቢት 27 ቀን 2018 የሚቆይ ሲሆን፤ እየታየ የሚገኘው ደግሞ ቦሌ፣ ብሪቲሽ ኢንተርናሽናል ስኩል አጠገብ ኬኬር ሆምስ 2ኛ ፎቅ በሚገኘው አርታዊ ጋለሪ ውስጥ ነው፡፡

## የግጥም ምሽት

“ወለሎ Night” የተሰኘ የግጥም ምሽት በነገው እለት ይካሄዳል፡፡ ይህ የግጥምና የጥበብ ምሽት ነገ ከምሽቱ 11፡00 ሰዓት ጀምሮ ቦሌ ቡልቡላ በሚገኘው ሪፈንቲ አፓርትመንት እንደሚካሄድ ተገልጿል። በመርሃ ግብሩ ላይ ወጣትና አንጋፋ ገጣሚያን ስራቸውን ያቀርባሉ ተብሏል፡፡

## ሙዚቃ

“አራዳ ነው ቤቷ“ የተሰኘ ነጠላ ዜማ ትናንት ምሽት ለአድማጭ ተመልካች ይፋ ሆነ፡፡ ይህ የድምፃዊ ዘርአብሩክ ሰማው የሙዚቃ ስራ በናሆም ሬከርድስ አማካኝት ለህዝብ ደርሷል፡፡ ድምጻዊው ከዚህ ቀደም ለአንጋፋና ወጣት ድምጻዊያን የግጥምና የዜማ ስራዎችን አበርክቷል፡፡ ከዚህ በፊት ምን ተረፈሽ፣ ገላጋይ እንዳትረሸው የተሰኙ ነጠላ ዜማዎችን ለህዝብ ያደረሰ ሲሆን አሁን ደግሞ ከረጅም ዓመታት በኋላ ይህን ስራ ይዞ ብቅ ብሏል፡፡ በሙዚቃ ስራው በግጥም ወንደሰን ይሁብ፣ በሙዚቃ ቅንብርና ሚክሲንግ ስማገኘው ሳሙኤል እና በዜማ ራሱ ዘርአብሩክ ሰማው ተሳትፈውበታል፡፡


## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። ቅዳሜ ከ7፡30 ሰዓት ጀምሮ ንጉስ አርማህ፣ 11፡30 ሰዓት ዴጊያ፣ እሁድ በ7፡30 ሰዓት ንጉሥ አርማህ ቴአትር እንዲሁም 11፡30 ሰዓት እምዩ ብረቷ ቴአትሮች በብሔራዊ ቴአትር ይታያሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው ከላይ ያለው ረድፍ 9+4+2=15 እንዲሁም ከታች ያለው ረድፍ ወደ ጎን 5+3+7=15 ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ በስተግራ ያለው የመጀመሪያው ረድፍ (ወደ ታች) 9+1+5=15 እንዲሁም በስተቀኝ ያለው 2+6+7=15 ይሆናል፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት የመሀለኛው ወደታች 4+8+3=15 እና ወደጎን 1+8+6=15 ነው፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **8** ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል። በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የአብሮነት ድምፅ

**በጊዜው አማረ**

መንዙማ ከሃይማኖታዊ ማስተማሪያነት ባለፈ፣ ጥልቅ የሆነ ማህበራዊ ፋይዳ ያለው ጥበብ ነው። መንዙማ "ነዘመ" (ደረደረ/ሰደረ) የሚል ትርጉም ካለው የአረብኛ ቃል የተወረሰ ሲሆን፣ ትርጉሙም በሥነ ስርዓት የተሰደረ ግጥም ወይም ውዳሴ ማለት ነው። በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ መንዙማ የእስልምናን አስተምህሮ፣ የነቢዩ መሐመድን ታሪክና የውልደት በዓል (መውሊድ)፣ እንዲሁም የደጋግ ሰዎችን ገድል ለሕዝቡ በቀላልና ማራኪ በሆነ መንገድ ለማድረስ የሚጠቅም ዋነኛ መሣሪያ ሆኖ ለዘመናት አገልግሏል።

ይህ ጥበብ በታሪክ ሂደት ውስጥ የኢትዮጵያ ሙስሊም ሊቃውንት ውስብስብ የሆኑ ትምህርቶችን ለሕዝብ ቀላል በሆነ መንገድ ለማስተማር የተጠቀሙበት ስልትም ነው። ሊቃውንቱ ጥንታዊ የአረብኛ ቃላትን ከአገሬው ቋንቋዎች ጋር በማዋሃድ ትውልድ ተሻጋሪ እውቀትን አስተላልፈውበታል።

የተለያዩ መሳሪዎችን በመጠቀም የሚቀርቡት እነዚህ መንፈሳዊ ውዳሴዎች፣ አድማጭን ከመሳብ ባለፈ የውስጥ ሰላምንና መንፈሳዊ መነሳሳትን የመፍጠር አቅም አላቸው። መንዙማ የግጥም ይዘቱ የሰው ልጅን ሥነ-ምግባር የሚያርም፣ ዓለማዊ ሕይወት አላፊ መሆኑን የሚያስታውስና ግብረ-ገብነትን የሚሰብክ፣ አብሮነትን የሚያስተምር፣ ፍቅርና አንድነትን የሚያጎላ፣ የመከባበርና መመካከር ፋይዳን ከፍ የሚያደርግ በመሆኑ እንደ ትልቅ የማህበረሰብና ሀገር ግንባታ መሳሪያ ይታያል።

መንዙማ ከማህበራዊ ፋይዳው አንጻር የአንድነትና የመረዳዳት፣ የአብሮነትና የመከባበር ምልክት ነው። በመውሊድ በዓላትና በተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥነ ስርዓቶች ላይ ሰዎች በጋራ በመሰብሰብ፣ አንዱ አውራጅ ሌላው ተቀባይ በመሆን የሚያሳዩት ስርዓት በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ትስስር ያጠናክራል። ይህም መንዙማ ከግል መንፈሳዊ እርካታ ባለፈ፣ የጋራ ማንነትንና ባህላዊ እሴትን ጠብቆ ለማቆየት የሚጫወተው ሚና የላቀ መሆኑን ያሳያል።

የመንዙማና ነሺዳ ባለሙያው አሚር መሐመድ የመንዙማ ጥቅሞች በኪታብ ላይ የተጻፉ ነገሮችን፣ የተለያዩ መጽሐፍት ላይ የተጻፉ ህጎችን፣ ትልልቅ ታሪኮችን... ጠቅለል ባለ ሃሳብና ልቦና ላይ በሚቀረጽ መልኩ ማስረዳት፣ ማስገንዘብ እና ማስተማር ነው ይላል፡፡ በመንዙማ ትልቅ ትምህርት ይሰጣል፡፡ የሚንጸባረቀው መልዕክትም የፈጣሪን ትእዛዝ መወጣትን፣ የቤተሰብን ሃቅ ማክበርን፣ በህይወት እያሉ የእናትና አባትን አደራ መወጣትን፣ አንድነትና አብሮነት ሊሆን ይችላል፡፡

ይህ የመንዙማ ጥበብ ግለሰቦች ከጎረቤቶቻቸውና ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባው ጠንካራ ትስስር፣ መረዳዳትና መተጋገዝ በስፋት ያስተምራል። በመሆኑም መንዙማን እንደ አንድ የማህበራዊ መመሪያ መጽሐፍ አድርጎ መመልከት ይቻላል።

..ኧ...መገን፣ መገን፣ መገን

የሰው ልጅ ወገን፤ የሰው ልጅ ዘመድ

የነጃሺ ልጅ፤ የሰይድ ቢላል

የታሪክ ዓምዱ መች ዘመም ይላል

ይፈርሳል አትበል ምኑ ይፈርሳል

በፍትህ ማህበር ጸንቶ ቆሞ ሳለ... የሚለው እና በሙንሺድ ወንድም ሷሊሕ "ሀገሬ" በሚል የተሰራው መንዙማ የሚያሳየውም ይህንኑ የሀገር አንድነትና አብሮነትን ነው፡፡

በእርግጥም የመቻቻልና የአብሮነት እሴቶች በመንዙማ ግጥሞች ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ዋና ጭብጦች ናቸው። በሀገራችን የሚታወቀው የመቻቻል ባህል በመንዙማ አማካኝነት ለትውልድ ሲተላለፍ ቆይቷል። ይህም ሰዎች እርስ በርስ በይቅርታና በአንድነት እንዲኖሩ በማሳሰብ፣ በማህበረሰቡ መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ በማስገንዘብ ረገድ ትልቅ አበርክቶ አለው።

በተጨማሪም መንዙማ በዕለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ ልንከተላቸው የሚገቡ ሥነ-ምግባሮችንና ልንተገብራቸው የሚገቡ በጎ ተግባራትን በዝርዝር ያስረዳል። በተቃራኒው ደግሞ ልንርቃቸው የሚገቡ መጥፎ ተግባራትን በማውገዝ፣ የሰው ልጅ ለፈጣሪውና ለወገኑ ታማኝ ሆኖ እንዲኖር ይመክራል።

ስለ ሞትና ስለ ዓለም አላፊነት የሚያስታውሱ የመንዙማ ስንኞች፣ ሰዎች በምድር ላይ በሚኖራቸው ቆይታ መልካም ስራን እንዲያበዙ ይገፋፋሉ። የነብዩ መሐመድን ስብዕና፣ ሥነ-ምግባርና ማህበራዊ ትስስርን የተመለከቱ ታሪኮች በዜማ ተቀናብረው ሲቀርቡ፣ ሰዎች መልዕክቱን በቀላሉ ተረድተው በህይወታቸው እንዲተገብሩት ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ።

መንዙማ ከመቻቻል፣ ከአብሮነት፣ ከይቅርታና ከሥነ- ምግባር አንጻር ያለው አበርክቶ ከፍተኛ ነው። ጥልቅ የሆኑ ማህበራዊ እሴቶች በግጥምና በዜማ ተቀናብረው መቅረባቸው፣ መልዕክቱ በሰዎች ልብ ውስጥ ረጅም ጊዜ እንዲቆይ ያደርገዋል። ይህ የሀገር በቀል እውቀት ዛሬም ድረስ ለማህበረሰባዊ ሰላምና አንድነት እንዲሁም ፍትህ ግንባታ እንደ ዋነኛ መሣሪያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

...ከፍ ዝቁን ተው ሁኑን እኩል በኩል

እስኪ አትናናቅ ወግ አትኮልኩል

የወንድምን ነፍስ ተው አትተንኩል... የሚለው የመንዙማ ስንኝ የሚያስረዳውና የሚያስተምረውም ይህንኑ ነው። የመንዙማና ነሺዳ ባለሙያ አሚር መሐመድ በበኩሉ ከዚህ ቀደም ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል በሰጠው አስተያየት መንዙማ ከሃይማኖትም ያለፈ ፋይዳ አለው፡፡ ትልልቅ የሀገር ባለውለታዎችን ለማስታወስ ይረዳል፡፡ የሀገር ፍቅርንም ይገልጻል፡፡ "ሃይማኖቱን በደንብ የሚያከብር ቤተሰቡን፣ ሀገሩን ያከብራል" የሚል መልክት በመንዙማ ይተላለፋል ይላል፡፡ ሁሉም ሃይማኖቶች የሚያዝዙት ደግሞ መከባበርን፣ አብሮነትን፣ ምክክርን፣ መዋደድን፣ ፍቅርንና መረዳዳትን ነው፡፡ ይህን በማንጸባረቅ ረገድ ደግሞ መንዙማ እጅግ ከፍተኛ ነው በማለት ያስረዳል፡፡

መንዙማ በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎችም ማህበረሰቦች ዘንድም በዜማው ለዛና በግጥሙ ጥልቀት የሚታወቅ ጥበብ ነው። ለዘመናት በመውሊድ፣ በሰርግና በተለያዩ ማህበራዊ መድረኮች ላይ ሰዎች በጋራ እንዲሰበሰቡና የአንድነት ስሜት እንዲሰማቸው ሲያደርግ ቆይቷል። ከዚህ አንጻር መንዙማ ኢትዮጵያ ለጀመረችው ሀገራዊ ምክክር ትልቅ አቅም መሆን የሚችል ሃብት ነው፡፡

ለሀገራዊ ምክክር ዋነኛው መነሻ ፍትህን፣ ይቅርታን፣ አብሮነትንና አንድነትን መገንባት እንደመሆኑ መጠን፣ መንዙማ ሰዎችን በአንድ ጥላ ስር የማሰባሰብ ተፈጥሯዊ ኃይል አለው። በመንዙማ መድረኮች ላይ የሚታየው አውራጅና ተቀባይ ሥነ ስርዓት፣ በራሱ የንግግርና የድምፅ ስምምነትን የሚያስተምር ነው። ይህ ደግሞ በሀገራዊ ምክክር ወቅት አንዱ ሌላውን እንዲያዳምጥ፣ የተለየ ድምፅ ያላቸው ወገኖች ደግሞ በጋራ ስምምነት ውስጥ እንዲካተቱ ለማድረግ እንደ ተምሳሌት መሆን የሚችል ስርዓት ነው፡፡

የማንኛውም ሀገራዊ ምክክር ማጠንጠኛ ያለፈውን ቁስል በይቅርታ መፈወስና ለወደፊቱ አብሮ ለመጓዝ መስማማት ነው። መንዙማ ደግሞ በይዘቱ የሰው ልጅን ሥነ- ምግባር የሚያርሙ መልዕክቶችን ይይዛል። በውስጡ የሚገኙት የይቅርታ፣ የትዕግስትና የርህራሄ ስንኞች ለምክክሩ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ናቸው።

መንዙማ ቂም በቀልን መተው እና ለሰው ልጅ ክብር መስጠትን ቅድሚያ ይሰጣል። በመንዙማ ውስጥ በዋናነት የሚተላለፈው "የሰው ልጅ ሁሉ ከጥላቻ ይልቅ ፍቅር ይገባዋል" የሚለው ትልቅ መልዕክት በጠረጴዛ ዙሪያ ለሚደረግ ውይይት በጎ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ይህን ሃሳብ የሚያጠናክርልን የወንድም ሷሊሕ መንዙማ ነው፡፡

በሀገር ልጅ ለዛ ተዋደድ አንተው

እኛ ከእነሱ መባባሉን ተው

ታረቅ ከራስህ ታረቅ ከሰው...፡፡

መንዙማ ስለ ሀገር ሰላምና ደህንነት የሚጸለይበት (ዱዓ የሚደረግበት) መድረክ ነው። "አላህ ሀገራችንን ሰላም ያድርግልን" የሚለውና ሌሎች መሰል የሀገር ፍቅር መግለጫዎች በዜማ ሲቀርቡ፣ ዜጎች ከጎሰኝነትና ከጠባብነት ተላቅቀው ስለ ትልቋ ሀገር እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል።

በሀገራዊ ምክክር ሂደት ውስጥ "ኢትዮጵያዊነትን" እና "የጋራ ማንነትን" ማጠናከር አንዱ ግብ ነው። መንዙማ የአገር በቀል ቋንቋዎችን በማቀናጀትና የአካባቢውን የዜማ ለዛ በመጠቀም፣ ልዩነትን እንደ ጌጥ የማየት ባህልን ያዳብራል። ይህ ደግሞ ምክክሩ "ልዩነታችንን አክብረን በአንድነትና በእኩልነት እንኑር" የሚለውን መርህ እንዲያሳካ ይረዳዋል።

በተጨማሪም መንዙማ በግጥሞቹ ውስጥ ስለ ማህበራዊ ኑሮ፣ ስለ ጎረቤት መብትና ስለ መረዳዳት በሰፊው ይተነትናል። አንድ ሰው ለብቻው ሳይሆን ከማህበረሰቡ ጋር ተሳስሮ መኖር እንዳለበት የሚያስተምሩት ስንኞች፣ ለምክክር ሂደቱ መሰረት የሆነውን አብሮነትና ፍቅርን፣ ይቅርታና አንድነትን ለመገንባት ያግዛሉ፡፡

መንዙማ ለሀገራዊ ምክክር፣ አብሮነትና አንድነት ያለው ፋይዳ ዘርፈ ብዙ ነው። ምክንያቱም መንዙማ የመቀራረብ መድረክ፣ የይቅርታ ትምህርት ቤት፣ የሀገር ፍቅር መግለጫና የማህበራዊ ትስስር ማጠናከሪያ ነው። ይህ ሀገር በቀል ጥበብ ከዘመናዊው የምክክር ሂደት ጋር ቢቀናጅ፣ ኢትዮጵያ ለምትፈልገው ዘላቂ ሰላምና እርቅ የበኩሉን ድርሻ ማበርከት ይችላል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

በጥዑም ዜማ የታጀበው መንዙማ ለዓለማዊ ህይወት ያለው አበርክቶ ትልቅ ነው

## የአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት

**ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች እንኳን ለ1447ኛው የኢድ - አል ፈጥር በዓል በሠላም አደረሳችሁ!**

በአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ኅብረተሰቡ ፈጣንና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ በዜጎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን የሀብትና የጊዜ ብክነት ማስቀረት እንዲሁም ለማህበራዊ ፍርድ ቤቶች በደንብ መተላለፍ የሚቀርቡላቸውን መዝገቦች በማየት ፈጣንና ፍትሐዊ የሆነ ውሳኔ እንዲሠጡ በማገዝ የአዲስ አበባ የህግ የበላይነትን እና ሰላምና ጸጥታ የተረጋገጠባት ከተማ ማድረግ የተቋሙ ተልዕኮ ነው፡፡ ይህን ተልዕኮውን ለማሳካት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ 121 ወረዳዎች ውስጥ በ112 ወረዳዎች የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ተደራሽ ሆነው ለነዋሪው ፈጣንና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል፡፡ ፍርድ ቤቶቹ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50(5) እና በአዋጅ ቁጥር 31/99 አንቀጽ 5 መሠረት ከብር 5,000 ያልበለጡ ክርክሮችን የመዳኘት የፍትሐ-ብሔር ስልጣን አላቸው፡፡

በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን የወጡትን ደንብ ቁጥር 150/2015፣ ደንብ ቁጥር 167/2016 እና በደንብ ቁጥር 180/2017 መሠረት የሚቀርቡላቸውን የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች መርምረው ፍትሐዊ ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቶቹ ያላቸው የፍትሐ-ብሔር የዳኝነት ሥልጣን በጣም ውስን መሆኑ አሁን ካለው የተሻለ የዳኝነት አገልግሎት ለኅብረተሰቡ እንዳይሰጡ አድርጓቸውል፡፡ ጉባዔ ጽ/ቤቱ ይህንን ችግር እስከ ወዲያኛው ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የመቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ እና አዲስ የአደረጃጀት ጥናት በማገባደድ ወደ ሥራ ለማስገባት አበክሮ እየሠራ ይገኛል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ይህ ጉዳይ የሚመለከታችሁ ባለድርሻ አካላት ኅብረተሰቡ በመኖሪያ አካባቢ ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት የማግኘት መብቱ እውን እንዲሆን የበኩላችሁን እንድትወጡ ስንል እንጠይቃለን፡፡

**ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች በዓሉ የሠላም፣ የጤና እና የብልጽግና እንዲሆንላቹ ይመኛል፡፡**

---

MIDROC INVESTMENT GROUP
ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ

# መልካም በዓል

**ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ- የሀገር ሀብት**

**እንኳን ለ1447ኛ ዓመተ ሂጂራ የኢድ አልፈጥር (ረመዳን) በዓል በሰላም አደረሳችሁ! እያለ መልካም ምኞቱን ይገልጻል!**

ግሩፑ በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በማዕድን፣ በንግድ፣ በሆስፒታሊቲ እንዲሁም በኮንስትራክሽንና ሪል እስቴት ዘርፎች የተደራጁ 45 ኩባንያዎችን ያቀፈና ከ80 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፈጠር የቻለ ነው።
ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ከትርፉ 10 በመቶውን በመመደብ ሀገራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል።

በተለያዩ አካባቢዎች ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማትን፣ መንገድ፣ ንጹህ ውሃ፣ የወንዝ ዳር ልማት፣ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታና ሌሎች ሥራዎችን እየሠራ ዜጎችን ተጠቃሚም አድርጓል።

ወደፊትም ለሀገራችን የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ አጠናክሮ ይቀጥላል።

# ልጆች፤ በዒድ አልፈጥር ስለሚደረግ የቤተሰብ ጥየቃ ምን ያህል ታውቃላችሁ?

**በሄለን ጥላሁን**

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? በየዕትሙ ለእናንተ የምናዘጋጃቸውን ጽሑፎች እያነበባችሁና እርስ በእርስ ሀሳብ እየተለዋወጣችሁ ነው የሚል እምነት አለን፡፡ ጎበዝ ልጆች፡፡ ዛሬ ደግሞ የዒድ አልፈጥር በዓልን ምክንያት በማድረግ ቤተሰብን ስለመዘየር (ስለመጠየቅ) መረጃ እናጋራችኋለን፡፡ ለዚህ ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ልጆችና የኃይማኖት አባት ለዝግጅት ክፍላችን የሰጡትን አስተያየት እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

ከግራ ወደ ቀኝ ኢክራም አህመድ፣ መሀመድ አንዋር እና ሂዳያ ፈድሉ

ኢክራም አህመድ እባላለሁ፡፡ በበዓል ዕለት የተገዛልኝን አልባሳትና ጫማ በመልበስ ዘመዶቼን ለመዘየር እሄዳለሁ። ሁልጊዜ በዓል ሲመጣ ወደ አክስቶቼ ቤት እሄዳለሁ፡፡ የእድሜ እኩዮቼንም በጣም ናፍቀውኝ ስለማገኛቸው በዓሉን በጉጉት ነው የምጠብቀው፡፡ እርስ በእርሳችን በስፍራው ላይ ስንገናኝ ፍቅር እንሰጣጣለን፡፡ ታላላቆቻችንም በዕለቱ ይመርቁናል፤ ዱአም ያደርጉልናል፡፡

ሂዳያ ፈድሉ እባላለሁ፡፡ ለበዓል ቤተሰብን የመዘየር ልምድ አለኝ፡፡ በአካል ማግኘት የማንችላቸውን ዘመዶቻችንን በስልክ የማገኛቸው ሲሆን ጎረቤቶቻችንን ደግሞ ሄጄ እዘይራቸዋለን፡፡ ስንዘይር ታድያ የሚበሉ ጣፋጭ ኬኮችንና ፍራፍሬዎችን በመያዝ ጭምር ነው፡፡

ከጎረቤት ጋር መጠያየቅ እንዲሁም የሩቅ ዘመዶችን ማስታወስ እንደሚገባ ሁልጊዜ እናትና አባቴ ይነግሩኛል፡፡ እኔም ለመጠየቅ በምንሄድበት ጊዜ ጓደኞቼን በመጠየቅ ይኸን ለማድረግ እሞክራለሁ፡፡

መህመድ አንዋር እባላለሁ፡፡ በዓል በመጣ ቁጥር የምናፍቀው ነገር ቢኖር የቆዩ ቤተሰቦቼን አግኝቶ መዘየር ነው፡፡ አያቴና አክስቴ በጣም ስለሚናፍቁኝና ሁልጊዜ አብሬያቸው ብሆን ብዬ ስለምመኝ የበዓል ቀኑን በጣም እናፍቀዋለሁ፡፡ እነሱም የሚያሳዩኝ ፍቅር ሁሌም እንድናፍቃቸው ያደርገኛል፡፡ ደስ በሚለው በበዓል ቀን ደስታችንን ለመካፈል እንደ ቤተሰብ መሰባሰብ እና መዘያየር የተለየ ድባብ እና ከፍተኛ የደስታ ስሜት አለው፡፡

ሼህ ማህሙድ ኢብራሂም እባላለሁ። በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 አንሷር መስጂድ ዋና ኢማም ነኝ፡፡ ልጆች፤ መዘየር ማለት ለመልካም ነገር ጉብኝት ማድረግ ማለትን ይወክላል፡፡ እንደ እስልምና ኃይማኖት ለመልካም ነገር ሰዎችን መጠየቅ በፈጣሪ ዘንድ ጥቅም ያስገኛል፡፡ ልጆች እናት፣ አባት፣ አጎት፣ አክስት፣ ወንድም፣ እህት፣ አያቶች እንዲሁም ቅርብ የሆኑ ሰዎች ጋር በመሄድ የመዘየር ሂደት ይከናወናል፡፡ አዲስ ልብስ ለብሳችሁ የናፈቋችሁን ወዳጆች በዚያ ዕለት ማግኘት ስሜቱ እጅግ የሚያስደስት ነው ፡፡

የመዘየር ጠቀሜታው ደግሞ እርስ በእርስ ዝምድናችሁን እንድታጠናክሩ ያግዛል፡፡ በቅዱስ ቁራን ላይ እንደተፃፈው "ሰዎች ሆይ የፈጠራችሁን አምላካችሁን ፍሩ፤ ታዘዙ፡፡ ዝምድናውን መቀጠል እንደሚጋባም በቁራን ላይ በግልፅ ተቀምጧል።" ታላላቆቻችንን ስንዘይራቸው የሚሰማቸው ደስታ ይህ ነው ተብሎ አይገለፅም፡፡ በምላሹም ፀሎት ይደረጋል፤ ምርቃትም ይሰጣል፡፡ ይህ ደግሞ ቀጣይ ለሚኖራችሁ የሕይወት ቆይታ መሠረት ይጥላል፡፡ በታላላቆቹ የተመረቀ ልጅ ስኬታማ እና በፈጣሪ ዘንድ የተወደደ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ልጆች ከዚህ ስርዓት የምትማሩት እንዴት ማህበራዊ ህይወታችሁን መምራት እንደምትችሉ ነው፡፡ ከታላላቆቻችሁ ጋር ስትገናኙ የሚሰጧችሁን ምክረ ሀሳቦች መተግበር ይኖርባችኋል፡፡ በፍፁም ትዕግስትና ሥነ ምግባር ውስጥ ራሳችሁን ማግኘት ይጠበቅባችኋል፡፡ ይህ ደግሞ ለተቀረው የሕይወት ዘመናችሁ ስንቅ ይሆናችኋል፡፡ ለጥየቃ በምትሄዱበት ወቅት ቢቻል የኑሮ ጫና ውስጥ ላለ ሰው ጠቃሚ ነገሮችን ይዞ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ባሻገር በእጦት ዙሪያ ችግር የሌለባቸው ዘመዶች ጋር ከሆነ የምትሄዱት ኬክ፣ ፍራፍሬ እና መሰል ነገሮችን ይዛችሁ መሄድ ትችላላችሁ፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**እግሩ አንድ ጭንቅላቱ ሦስት**

**መልስ፡-** *ሀ. መንሽ*

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**እንዲህ ቢሏት አትታይ ፤ እንዲያ ቢሏት አትታይ**

ሀ. ጆሮ

ለ. አይጥ

ሐ. ቀበሮ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የተገለጠው የስራ ዕድል ምንጭ

**በይግለጡ ጓዴ**

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 የሚኖረው ወጣት ጀምበሩ ተሰጋ፣ የከተማ ግብርና እንዴት የአንድን ወጣት ሕይወት እንደሚቀይር ሕያው ምስክር ነው። ትምህርቱን አጠናቅቆ ያለ ሥራ ተቀምጦ የነበረው ጀምበሩ፣ በ2016 ዓ.ም በተፈጠረለት ዕድል በመታገዝ ዛሬ ቲማቲም፣ ጎመንና ሽንኩርት በማልማት ላይ ይገኛል። “ወጣቶች ሥራ ሳይመርጡ ወደዚህ ዘርፍ ቢገቡ ራሳቸውን መለወጥ ይችላሉ፤ እኔ ያገኘሁት ለውጥ በተጨባጭ የሚታይ ነውና ሁሉም የዕድሉ ተጠቃሚ ቢሆን ደስ ይለኛል” የሚለው ጀምበሩ፣ ዘርፉ ለሥራ አጥ ወጣቶች ትልቅ ተስፋ መሆኑን ያስረዳል።

በተመሳሳይ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ነዋሪ የሆኑት አቶ ፍቅሩ ገብሬ፣ በአትክልት ልማት ዘርፍ ውጤታማ መሆን የቻሉ አርሶ አደር ናቸው። ቆስጣ፣ ሀበሻ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቀይ ስርና ዝኩኒን በማምረት በዓመት እስከ አራት ጊዜ ምርት ያገኛሉ። አቶ ፍቅሩ ከራሳቸው ባለፈ ለሦስት ሌሎች ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል። የዚሁ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ነዋሪ የሆኑት አቶ በርጋ ሽኩሪም ድንችና የተለያዩ አትክልቶችን በማምረት የከተማ ግብርና ሰፊ የሥራ ዕድል ፈጣሪ መሆኑን በተግባር እያሳዩ ይገኛሉ።

በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የከተሞች መስፋፋትና የሕዝብ ቁጥር መጨመር የምግብ ዋስትናን አሳሳቢ ከማድረጉ ባለፈ፣ ለሥራ አጥ ዜጎች አዲስ አማራጭ መፈለግን ግድ ብሏል። በዚህ ረገድ የከተማ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል ሲል የተባበሩት መንግሥታት የግብርናና ምግብ ድርጅት (ፋኦ) መረጃ ያመለክታል።

ፋኦ እ.ኤ.አ በ2023 ባወጣው መረጃ መሠረት፣ በአሁኑ ወቅት ከ400 ሚሊዮን በላይ የዓለም ከተሞች ነዋሪዎች በአትክልትና ፍራፍሬ ግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩ ሲሆን፣ ይህም በከተሞች የሚታየውን የሥራ አጥነት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰው ይገኛል። ዘርፉ ከምርት እስከ ግብይት ባለው ሰንሰለት ውስጥ ለወጣቶችና ለሴቶች ሰፊ የገቢ ምንጭ በመሆን እያገለገለ ነው።

በዚህ ረገድ የኩባዋ መዲና ሃቫና፣ ሲንጋፖር፣ ኒው ዮርክ፣ ቶክዮ፣ ባንግኮክ መልካም ተሞክሮ ያላቸው ከተሞች ናቸው። ሃቫና በከተማ ግብርና አማካኝነት ከ300 ሺህ በላይ ቋሚ የሥራ ዕድሎችን መፍጠር የቻለች ሲሆን፣ የከተማዋን የአትክልት ፍላጎት 90 በመቶ በራሷ ምርት መሸፈን ችላለች። በሌላ በኩል ሲንጋፖር ያላትን ውስን መሬት በአቀባዊ ግብርና (Vertical Farming) እና በከፍተኛ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ለቴክኒክ ባለሙያዎችና ለሥራ ፈጣሪዎች አዳዲስ የሥራ ዘርፎችን ከፍታለች። እነዚህ ከተሞች ግብርናን ከህንፃዎች ጣሪያና ከጓሮ ባለፈ ወደ ኢንዱስትሪ ደረጃ በማሳደጋቸው፣ የዜጎቻቸውን የኢኮኖሚ አቅም ከመገንባት ባለፈ ለከተማ ውበትና ለአካባቢ ጥበቃ ትልቅ ስኬት አስመዝግበዋል።



የከተማ ግብርና ለበርካታ ወገኖች የስራ ዕድል ፈጥሯል

ፎቶ- ከገፀ ድር

> “የከተማ ግብርና ከባህላዊው እርሻ ወጣ ባለ መልኩ በውስን ቦታ ላይ፣ በቴክኖሎጂና በፈጠራ የታገዘ ምርት የማምረት ጥበብ ነው፤ ወጣቶችና ሴቶች በጓሮ አትክልት፣ በችግኝ ማፍላትና በእንጉዳይ ልማት በመሰማራት የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን እያረጋገጡ ነው።”

የእነዚህ ከተሞች ተሞክሮ እንደሚያሳየው፣ የከተማ ግብርና ከምግብ ፍጆታ ባለፈ ዘርፈ-ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል። የምርት ወጪን በመቀነስ የኑሮ ውድነትን ማረጋጋታቸው፣ የትራንስፖርት ብክለትን መግታታቸውና የከተማ ሙቀትን መቀነሳቸው ተጠቃሽ ስኬቶቻቸው ናቸው። አዲስ አበባም ይህንን ዓለም አቀፍ ተሞክሮ መነሻ በማድረግ፣ ያላትን ክፍት ቦታዎችና የሰው ኃይል በማስተባበር የከተማ ግብርናን ለሥራ ዕድል ፈጠራ ትጠቀምበታለች። ይህ የዘርፉ ዕድገት ለከተማዋ ነዋሪዎች የሥራ ዕድልን ለመፍጠር ወሳኝ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል።

የከተማ ግብርና ከባህላዊው እርሻ ወጣ ባለ መልኩ በውስን ቦታ ላይ፣ በቴክኖሎጂና በፈጠራ የታገዘ ምርት የማምረት ጥበብ ነው። የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚመክሩት፣ በእጽዋትና በአትክልት እንክብካቤ ላይ መሰማራት ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ከመሆኑም በላይ፣ ለአካባቢ ጥበቃና ለምግብ ዋስትና መረጋገጥ የማይተካ ሚና አለው። በተለይም ወጣቶችና ሴቶች በጓሮ አትክልት፣ በችግኝ ማፍላትና በእንጉዳይ ልማት በመሰማራት የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን እያረጋገጡ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ ዘርፉ እያመጣ ያለው ለውጥ የሚደነቅ ነው። በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የሆልቲካልቸር ባለሙያ የሆኑት ወይዘሮ መሰረት መካሻ እንደሚሉት፣ በስድስት ወራት ውስጥ ብቻ በክፍለ ከተማው ለ503 ዜጎች በእጽዋት ዘርፍ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል። ይህ እንቅስቃሴ ነዋሪዎች ትኩስ አትክልትን ከደጃቸው እንዲያገኙ ከማስቻሉም በላይ የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አለው።

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማም በተመሳሳይ መልኩ 52 ጊዜያዊና 163 ቋሚ የሥራ ዕድሎች መፈጠራቸውን የዘርፉ ባለሙያ አቶ ጠና ነገራ ገልጸዋል። እንደ ሀገርና እንደ ከተማ ትልቅ ፈተና የሆነውን የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ለመቅረፍ እንዲህ ያሉ የጓሮ አትክልት ልማቶች መፍትሔ እየሆኑ ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የሥራ ዕድል ፈጠራ ፎካል ፐርሰን አቶ ቢንያም አድማሱ እንዳብራሩት፣ በእጽዋት ሀብት ልማት ዘርፍ ብቻ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ነዋሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል። ከዚህ ውስጥ በአትክልት ልማት 5 ሺህ 646፣ በችግኝ ማፍላት 305፣ በእንጉዳይና ኮምፖስት ዝግጅትም በርካታ ዜጎች ተሳታፊ ሆነዋል።

በ2017 በጀት ዓመት ለ25 ሺህ 221 ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ፣ በ8 ወራት ውስጥ ብቻ 20 ሺህ 455 ወጣቶችን ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል። ይህም የከተማ ግብርና ተመራጭነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ያሳያል።

አዲስ አበባ ዛሬ በእንቁላል፣ በሥጋ፣ በወተትና በእጽዋት ልማት ተጨባጭ ለውጥ እያሳየች ነው። የከተማ ቆሻሻን ወደ ተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) በመቀየር ለግብርና ግብዓትነት የመጠቀም ሥርዓት መዘርጋቱ ደግሞ ዘርፉ ዘላቂነት እንዲኖረው ያደርገዋል።

ወጣቶችና ሴቶች ይህንን ሰፊ ዕድል በመጠቀም፣ ሥራ ሳይመርጡና በቴክኖሎጂ ታግዘው ወደ ከተማ ግብርናው ቢገቡ፣ የግል ገቢያቸውን ከማሳደግ ባለፈ የከተማዋን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት ትልቅ አቅም መሆን ይችላሉ። የግብርና ሚኒስቴር መረጃ እንደሚጠቁመው፣ ዘርፉ የዜጎችን የማምረት አቅም ከማሳደግ ባለፈ፣ ለተመጣጠነ ምግብ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

# ጥንቃቄ የሚያሻቸው የበዓል ሰሞን ተግባራት

- ማህበረሰቡ በበዓላት ወቅት ብቻም ሳይሆን በማንኛውም ጊዜ ለራሱ ጤንነት ሲል አካባቢውን ከብክለት መጠበቅ እንዳለበት ተጠቁሟል

**በፋንታነሽ ተፈራ**

በዓላት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ልዩ ትርጉም አላቸው፡፡ ፍቅር፣ አንድነት እና መረዳዳት የሚገለፅባቸው፣ ደምቀውና ደስታን ዘርተው የሚውሉ ቀናት ናቸው። ሆኖም በዓላትን ለማድመቅ የምናከናውናቸው ተግባራት የአካባቢ ብክለትን ጨምሮ ዘርፈ ብዙ ችግሮች እንዳያስከትሉ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ የሚታረዱ የእንስሳት ተረፈ ምርቶች፣ የቤት ውስጥ ቆሻሻዎች እና የፕላስቲክ ውጤቶች በአግባቡ ካልተወገዱ አየር እንዲበከል፤ ለተለያየ በሽታ እንድንጋለጥ፤ የውሃ ማፋሰሻ መስመሮች እንዲዘጉ… በማድረግ ለጉዳት ይዳርጋሉ፡፡ በአዲስ አበባም መሰል የበዓል ዝግጅት እንደሚደረጉና ተግባራቱ ነዋሪዎችን እና ከተማዋን ለተለያዩ ችግሮች እያጋለጡ እንደሆነ የዝግጅት ክፍላችን ካነጋገራቸው ሰዎች ያሰባሰበው መረጃ ያመላክታል፡፡

የከተማዋ ነዋሪ የሆኑት አቶ አደም ሙስጠፋ በጉዳዩ ላይ በሰጡት አስተያየት፣ “በዓላት ሲመጡ በደስታ ለማሳለፍ የተለያዩ ነገሮች ገዝተን ወደ ቤት እናስገባለን፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በግ ማረድ ወይም ቅርጫ ማስገባት ይጠቀሳል። ለምሳሌ፡- እኔ ለዒድ አል ፈጥርም ሆነ አረፋ በዓል በግ አርዳለሁ፡፡ ከዚህ በፊት ፈርሱን እና ደሙን ቱቦ ውስጥ እንደፋዋለን፡፡ ይህም ለብዙ ቀናት ቱቦው ተደፍኖ ውሃ እንዳያልፍ ያደርግ ነበር። አሁን ግን ከዚህ ትምህርት በመውሰድ እንዳይሸትም ሆነ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች እንዳይዘጉ በግቢያችን ጥግ ላይ ጉድጓድ ቆፍረን መቅበር ጀምረናል” ይላሉ፡፡

“የእንስሳት ተረፈ ምርት አለአግባብ ውጭ ላይ ከተጣለ ዝንቦች እንዲራቡ ያደርጋል፤ ውሾችም ይበትኑታል” የሚሉት አቶ አደም ሙስጠፋ፤ ይህ እንዳይሆን ቆሻሻን በየቦታው ባለመጣልና በአግባቡ በማስወገድ ራሳችንን ከበሽታ፣ አካባቢያችንን ደግሞ ከብክለት እንጠብቅ ይላሉ፡፡

በበዓላትም ሆነ በመደበኛ ቀናት ቆሻሻን በአግባቡ እንደሚያስወግዱ የነገሩን ደግሞ ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ ወይዘሮ ሰላም ክፍሌ ናቸው። “ከወትሮው በተለየ በበዓላት ወቅት የቆሻሻ መጠኑ ይጨምራል፡፡ በዚህ ጊዜ ከዚህ በፊት እንደማደርገው የሚበሰብሱና የማይበሰብሱ በመለየት በቆሻሻ ማዳበሪያ ውስጥ አስቀምጣለሁ። የጽዳት ሰራተኞች ሲመጡም አውጥቼ እሰጣለሁ፡፡ ግቢ ውስጥ በግ በምናርድበት ወቅትም የታረደበትን ስፍራ በውሃና በበረኪና አፀዳለሁ” ሲሉ ቆሻሻን በአግባቡ በማስወገድ የራሳቸውንም ሆነ የቤተሰባቸውን ጤና እንደሚጠብቁ ተናግረዋል፡፡

በበዓላት ወቅት የሚደረጉ የእርድና መሰል ተግባራት አካባቢ ላይ ምን ያክል ተጽዕኖ እንደሚያሳድር እና ከማህበረሰቡም ምን እንደሚጠበቅ ማብራሪያ የሰጡት የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ብክለት ክትትልና ቁጥጥር ተፅዕኖ ግምገማ ቡድን መሪ ወይዘሮ ሰናይት ተስፋዬ



ፎቶ- ከፋይል

የወንዝ ዳርቻ እና የኮሪደር ልማትን ከአካባቢ ብክለት እንዲጠበቁ ማድረግ የሁሉም ኃላፊነት ነው

ለአካባቢ ብክለት ስለሚያጋልጡ ነገሮች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እየተሰራ ነው። በዘንድሮው በጀት ዓመት በስምንት ወራት ውስጥ በተለያዩ አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ለ112 ሺህ 518 የህብረተሰብ ክፍሎች በገፅ ለገፅ የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተሰርቷል።

ናቸው፡፡ ቡድን መሪዋ በማብራሪያቸው እንደገለጹት፣ ከወትሮው በተለየ ከበዓላት ጋር በተያያዘ በየቤቱ የሚታረዱ እንስሳት ቁጥር ይጨምራል፡፡ በዚህም ፈርስ፣ ቆዳ፣ ደም እና ቀንድ የመሳሰሉ ተረፈ ምርቶች ይመነጫሉ፡፡

የተለያዩ እቃዎች የሚገዙባቸው ማሸጊያዎች፣ ቤታችንን የምናስውብባቸው ነገሮች፣ የመጠጥ ጠርሙሶችና ሃይላንዶች፣ ከሸንኩርት ልጣጭ ጀምሮ እስከ ቄጤማ ያለው ተረፈ ምርት በከፍተኛ መጠን ይመነጫል፡፡ እነዚህ ተረፈ ምርቶች በአግባቡ ካልተወገዱ ከፍተኛ የብክለት ምንጭ ይሆናሉ። በባህላችን ለበዓላት ሰዎች ሰብሰብ ብለው ቅርጫ ይከፋፈላሉ፡፡ ይህም አብዛኛውን ጊዜ በህጋዊ መንገድ ወይም በቄራዎች ሳይሆን ሰፈር ውስጥ በህገ ወጥ መንገድ ነው እርድ የሚከናወነው፡፡ ከታረዱት እንስሳት የሚወጣውን ተረፈ ምርት አንዳንድ የማህበረሰብ ክፍሎች ውሃ ማፋሰሻ መስመሮች (ቱቦዎች) ውስጥ ይደፋሉ፡፡ ይህ ሲሆን የከተማዋን የፍሳሽ ማስወገጃዎች ይዘጋሉ። እነዚህ የፍሳሽ ማስወገጃዎች ከተዘጉ ደግሞ ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት መተላለፊያ ስለሚያጣ የጎርፍ አደጋ ያስከትላል፡፡

ከዚህ ባለፈም መጥፎ ጠረን ስለሚያመጣ ለዝንብና መሰል ነፍሳት መራቢያ ይሆናል፡፡ የውሃ ብክለት ይፈጥራል። የአካባቢን እይታም ያስተጓጉላል፡፡ ይህ እንዳይሆን በተቻለ መጠን እርድ ሲከናወን በህጋዊ መንገድ ማከናወን፣ የሚመለከተው አካልም ሌሎች ቆሻሻዎችን በአግባቡ ሰብስቦ እንዲያነሳ በጥንቃቄ ማስቀመጥ ተገቢ መሆኑን ቡድን መሪዋ ገልጸዋል፡፡

“ብክለትን መከላከል ከቤትና ከአካባቢ ይጀምራል” ያሉት ወይዘሮ ሰናይት፤ ይህን ማህበረሰቡ ተግባራዊ እንዲያደርገው የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በዋናነት ትኩረት ሰጥቶ ግንዛቤ ፈጠራ ላይ እየሰራ ነው፡፡ ይህም ሲባል አጠቃላይ በከተማዋ በተለያየ ጊዜ ግንዛቤ ይሰጣል፡፡ በተገኘው መድረክ ሁሉ ለአካባቢ ብክለት የሚያጋልጡ ነገሮች ምን እንደሆኑ፣ በምን መንገድ መወገድ እንዳለባቸው እንዲሁም የሚያስከትሉት ጉዳት ጭምር እንዲያውቁ የማድረጉ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ በመደበኛ እቅድ በዘንድሮው በጀት ዓመት በስምንት ወራት ውስጥ በተለያዩ አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ለ112 ሺህ 518 የህብረተሰብ ክፍሎች በገፅ ለገፅ የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከንቅናቄ ስራዎች አንጻር ከ2017 ዓ.ም ጀምሮ በወንዝ ብክለት መከላከል ለ1 ሚሊዮን 408 ሺህ 693፣ በፅዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ ለ1 ሚሊዮን 67 ሺህ 161 የህብረተሰብ ክፍሎች የገፅ ለገፅን ጨምሮ በተለያዩ መንገዶች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

ግንዛቤ ፈጠራው በክፍለ ከተማ፣ በወረዳ እና በብሎክ ቤት ለቤት፣ በቅስቀሳ እንዲሁም በብሮሸር ጭምር ይሰጣል። በዚህ መሰረት የፍሳሽ፣ የአየር፣ የሽታ እንዲሁም የድምፅ ብክለት ደረሰብን ብለው የሚመጡ አቤቱታዎች መቀነስ መቻላቸው እና የከተማዋ አብዛኞቹ አካባቢዎች ንፁህ መሆናቸው ውጤታማ ለመሆናችን ምስክር ናቸው፡፡ ከዚህ በፊት ብክለት ሲያጋጥም የት ማመልከት እንኳን እንዳለባቸው ግንዛቤው ያልነበራቸው የማህበረሰብ ክፍሎች አሁን ግንዛቤው አላቸው፡፡

ሌላኛው ብክለት ሲያጋጥም በ6713 ነፃ የስልክ መስመር ደውለው እንዲያሳወቁ ተደርጓል፡፡ በዚህ መስመርም ማህበረሰቡ ደውሎ ያሳውቃል፤ ያጋጠሙ የብክለት ችግሮችን ይናገራል፡፡ ህብረተሰቡም አካባቢው ተበክሎ እያየ ዝም አይልም፡፡

በአሁኑ ወቅት የላስቲክ አጠቃቀማችን እየቀነሰ መጥቷል ያሉት ወይዘሮ ሰናይት፤ ማህበረሰቡ በበዓላት ወቅት ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ጊዜ ቆሻሻ ጎድጓዳ ቦታዎች እንዲሁም ወንዝ ዳር ከመጣል መከልከል አለበት፡፡ ምክንያቱም በተለይ እንደ አዲስ አበባ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች ከተዘጉ ጎርፉ አደጋ የሚያደርሰው እራሱ ነዋሪው ላይ ነው፡፡

እንደ ቡድን መሪዋ ገለጻ፣ መስሪያ ቤቱ ከአዲስ አበባ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ ከደንብ ማስከበር ባለስልጣን፣ ከውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣ አዲስ አበባ ፖሊስ እንዲሁም ከአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ጋር እየሰራ ይገኛል፡፡ አዳዲስ መረጃዎች ሲኖሩም ለእነዚህ አካላት በማሳወቅ ለማህበረሰቡ እንዲያደርሱ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ማህበረሰቡ በበዓላት ወቅት ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ጊዜ ለራሱ ጤንነት ሲል አካባቢውን ከብክለት መጠበቅ እንዳለበት የሚናገሩት ወይዘሮ ሰናይት፤ የእንስሳት እርድን በህጋዊ መንገድ መፈፀም፣ ክፍት ቦታዎችና ቱቦዎች ባሉበት ቦታዎች ጨለማን ተገን አድርጎ ቆሻሻን ከመጣል መቆጠብ ተገቢ እንደሆነ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የከተማዋ ንፅህና እና የማህበረሰቡ ጤና እንዲጠበቅ እንዲሁም ሳቢና ማራኪ ሆና እንድትታይ ከአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በቅንጅት እንደሚሰሩ የነገሩን ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የአገልግሎት አሰጣጥ ዳይሬክተር አቶ ግርማ ኃይሉ ናቸው፡፡ ኤጀንሲው በዓመቱ ውስጥ ያሉ በዓላትንና የአደባባይ ሁነቶችን ታሳቢ በማድረግ ዓመታዊ ዕቅዶችን ያቅዳል። በእቅዱ መሰረትም ማህበረሰቡ በምን መንገድ ቆሻሻን እንደሚያስወግድ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

ዳይሬክተሩ እንደገለፁት፤ በበዓላትም ይሁን በሌሎች ጊዜያት ማህበረሰቡ የሚያመነጨውን ቆሻሻ በአግባቡ እንዲይዝና እንዲያስወግድ በየተቋማቱና ቤት ለቤት የግንዛቤ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም ኤጀንሲው የሚሰራቸውን ስራዎች በዶክመንተሪ መልክ በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እናስተላልፋለን፡፡ የአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር ባለስልጣንም ግንዛቤ በመስጠትና ግንዛቤው ኖሯቸው ቆሻሻን በአግባቡ የማይዙና የማያስወግዱ ሲኖሩ ተጠያቂነትን በማስፈን እገዛ ያደርግልናል፡፡ ስራዎችን በቅንጅት መስራት የስራ ጫናን ያቀልላል። ለከተማዋም ፅዳት ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በፊት በቀን ሶስት ጊዜ ይሰበሰብ የነበረውን ቆሻሻን በአሁኑ ወቅት ምሽትንም በመጨመር አራት ጊዜ እንዲሰበሰብ ተደርጓል። ይህ ስራ ከተማዋ አሁን ያለችበትን ገፅታ እንድትይዝና ቱሪስቶችን የምትስብ እንድትሆን አድርጓታል ነው ያሉት አቶ ግርማ፡፡

በበዓላት ወቅት የእንስሳት እርድና መሰል ተረፈ ምርቶች በየቦታው እንዳይጣሉ ለየት ባለ ሁኔታ የየወረዳዎችና ክፍለ ከተሞች ፅዳት አስተዳደር ፅህፈት ቤቶች በቋሚነት ግንዛቤውን ይፈጥራሉ። ትናንት ለተከበረው የዒድ አል ፈጥር በዓልም ይህንኑ ነው ያደረግነው። በዚህም ግንዛቤው ሳይኖረው ከ10 ዓመት በፊት ተረፈ ምርቶችን በየወንዙና መንገድ ዳርቻዎች የሚጥል ማህበረሰብን ማስቀረት ተችሏል፡፡

በከተማዋ 76 በመቶ የሚሆነው ቆሻሻ የሚመነጨው ከመኖሪያ ቤትና አካባቢ መሆኑን የነገሩን አቶ ግርማ፤ ስለዚህ ህብረተሰቡ ከዚህ በፊት የሚያደርገውን ቆሻሻን በአግባቡ የመያዝና የማስወገድ ተግባር ወደፊትም አጠናክሮ ይቀጥል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

# ማስታወቂያ

## የቅጥር ማስታወቂያ

### የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔታ | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **በቴክኖሎጂ ዘርፍ ፕሮዳክሽን ዳይሬክቶሬት** | | | | | | | | | | |
| 1 | ከፍተኛ የፕሮግራም ካሜራ ባለሙያ | X | ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ ቢ.ኤስ.ሲ | 6/4 ዓመት | በፎቶ ግራፍ፣ ቪዲዮ ግራፊና በሲኒማ ቶግራፊ፣ በኤሌክትሪክሲቲ፣ ICT Film Directing በኤሌክትሪካል፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኮምፒውተር ሳይንስ ወይም ተዛማች የትምህርት ዘርፍ | አ/18.573 እስከ አ/18.577 አ/18.590 አ/18.591 | 7 | ቋሚ | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አአ |
| 2 | የመስክ ካሜራ ባለሙያ | VIII | ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ ቢ.ኤስ.ሲ | 4/2 ዓመት | በፎቶ ግራፍ፣ ቪዲዮግራፊና በሲኒማ ቶግራፊ፣ በኤሌክትሪክሲቲ፣ ICT Film Directing በኤሌክትሪካል፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኮምፒውተር ሳይንስ ወይም ተዛማች የትምህርት ዘርፍ | አ/18.592 አ/18.594 አ/18.599 | 3 | ቋሚ | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አአ |
| **ለቢዝነስና ገበያ ልማት ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 3 | የማርኬቲንግ፣ ፕሮሞሽንና የማስታወቂያ ባለሙያዎች | -- | በማንኛውም የትምህርት ዝግጅትና ደረጃ ሆኖ በማርኬቲንግ ና ፕሮሞሽን ላይ በቂ ዕውቀት፣ ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ እና ክህሎት ያላቸው | በዘርፉ ልምድና ክህሎት ያላቸው እንዲሁም ሞዴል አርቲስቶች ጭምር መሳተፍ ይችላሉ | በማንኛውም የትምህርት መስክ በማርኬቲንግ ና ፕሮሞሽን ላይ በቂ ዕውቀት፣ ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ አለን የምትሉ ሁሉ እንዲሁም በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ በመስራት በዘርፉ ልምድ ያላችሁ ላይ ልዩ ተሰጥኦ ያለዉ /ያላት | -- | 4 | በታለንት ግዢ | በድርድር | አአ |
| 4 | ከፍተኛ የብራንዲንግ ባለሙያ | IX | ቢ.ኤ/ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በማርኬቲንግ ማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በቢዝነስ ማኔጅመንትና ተመሳሳይ የትምህርት መስክ ወይም በተዛማጅ የትምህርት መስክ | አ/18.1069 | 1 | ቋሚ | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አአ |
| 5 | ጀማሪ የማርኬቲንግና ሽያጭ ባለሙያ | V | ቢ.ኤ.ዲግሪ | 0 ዓመት | በማርኬቲንግ ማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በቢዝነስ ማኔጅመንት | አ/18.1083 | 1 | ቋሚ | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አአ |

**ማሳሰቢያ፤**

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 10(አስር) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት መረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ሀብት ስራ አመራር ዲፓርትመንት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርቡ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳብ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር **ቀጥተኛ** መሆን አለበት፡፡
4. በቴክኒክና ሙያ/ሌቭል የሚወዳደሩ የብቃት ማረጋገጫ /COC/ ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የምዝገባው ቀን ከመጋቢት 14 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ መጋቢት 25 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ነው፡፡
6. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
7. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን ስልክ ቁጥር 011551848

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ ነጃ ሰማን ሽፋ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA000080206507030002 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 401 በአቶ ባሩዴ ዘለቀ ሞገ ስም የተመዘገበው የይዞታ ካርታ ቁጥር 18655 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 09/07/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

## የኢድ ... ከገጽ 6 የዞረ

የእምነቱ ተከታዮች ዘካ ለማሰባሰብ በሚዋቀረው ኮሚቴ ወጣቶች አባል በመሆን፣ ከማህበረሰቡ በተሰበሰበው ገንዘብ ከዱቄት ፋብሪካዎች ዱቄት ይገዛሉ፡፡ ችግረኛ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲመዘገቡ ከተደረገ በኋላ እንደተገዛው የዱቄት መጠን አስር ወይም አምስት ሊሆን ይችላል፤ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች በወጣቶች አማካኝነት ይታደላል። ባለፈው ዓመት በነበረው የኢድ በዓል እስከ 20 ኩንታል ዱቄት ተሰባስቦ ድጋፍ ፈላጊ ለሆኑ ዜጎች እንዲሰራጭ በማድረግ በዓሉን በደስታ እንዲያሳልፉ ተደርጓል፡፡ በዘንድሮ በዓልም ይህ ተግባር ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በኢድ አልፐር በዓል የሚደረገው የመደጋገፍ እሴት በእለት ተለት ህይወት ሊተገበር እንደሚገባ ሼህ አሊ ይናገራሉ። "ዘካ መስጠት ግዴታ ነው፡፡ የሰዎችን ማህበራዊ ችግር ያቃልላል፡፡ የነብዩ መሐመድ መርህንም መከተል ነው፡፡ የእርሳቸው መርህ አንዱ ለአንዱ ማዘን ነው፡፡ ለሰው የማያዝን ከእኔ አይደለም፤ አላህ አያዝንለትም" ብለዋል፡፡ ይህንንም ህዝበ ሙስሊሙ እንዲተገብረው ማታ ከሶላት በፊት በየመስጂዱ ትምህርት ይሰጣል፡፡

አቅም የሚያንሳቸው፣ በችግር ምክንያት ደስታ የራቀቸው ሰዎች፣ ራሳችን ደስታ እንዳገኘን ሌሎችም ደስ እንዲላቸው ትንሽና ትልቅ ሳይል የዘካ ግዴታውን መወጣት ይኖርብናል፡፡ ነብዩ መሐመድ 'በአንተ ቤት ደስታ ኖሮ በጎረቤትህ ከሌለ፤ በቤትህ እየበላህ፤ ጎረቤትህ የሚራብ ከሆነ አንተ ከእኔ አይደለህም፤ ነገ በአላህ ዘንድ ያስቀጣል" እንዳሉት በተግባር መገለጥ እንዳለበት ምክራቸውን ለግሰዋል፡፡

በጥቅሉ ዘካ ከራስ በፊት ለሌላው ማሰብን የሚያስተምር ሥርዓት ነው። እንዲህ ዓይነት እሴቶች አካል ጉዳተኞችን፣ ድኾችን፣ ዐቅመ ደካሞችን፣ አረጋውያንን፣ ሕጻናትንና የተለያዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ማህበራዊ ችግሮች በማቃለል ትስስርን፣ መደጋገፍንና መተባበርን የሚያጠናክር በመሆኑ ትውልዱን በማስተማር አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡

በወ/ሮ አበበች ወ/ማርያም ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ4/16/2/15/1925/19375/01 የተሰጠበት ቀን 23/04/2005 ዓ.ም የቦታው ስፋት 509 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 09 የሆነው መኖሪያ ቤት በወ/ሮ አበበች ወ/ማርያም ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ4/16/2/15/1925/19375/01 የተሰጠበት ቀን 23/04/2005 ዓ.ም የቦታው ስፋት 509 ካ.ሜ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታውን(ቤቱን) በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ መሆኑን እየገለጽን የማስታወቂያው ወጪ በባለጉዳዩ የሚሸፈን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ወልደማርያም ሀለፎም ገብረተክሌ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070404015 በሴሪ ቁጥር L 019150 በወልደማርያም ሀለፎም ገብረተክሌ ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጇ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ ዳንኤል ሀ/ማርያም ክብረት ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር ጀሞ1-01/757/23463/01 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ ወ/ት አማረች ፈለቀ በላይነህ በየካ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 9999/1 የካርታ ቁጥር የካ/256230/13 ሴሪ ቁጥር 0144077 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች በወ/ሮ በብዙነሽ መኩሪያ ለማ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070403331 በሴሪ ቁጥር 0233077 በብዙነሽ መኩሪያ ለማ ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጇ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች ሰብለ ታደሰ ገብሩ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070404012 በሴሪ ቁጥር L 017811 በሰብለ ታደሰ ገብሩ ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጇ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ 4 ካርታ ቁጥር 01082/1 በሴሪ ቁጥር 192723 አቶ በእምነት ጋሻው ማሞ የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ካለ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ እንድታሳውቁን እናሳውቃለን።

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ጃሌ ዴሬሳ በካኮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 07 ነዋሪ የሆኑት የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000100701628 የሴሪ ቁጥር L-035367 በወ/ሮ ጃሌ ዴሬሳ ወጪ የተደረገ ካርታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለው/ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትክ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፡- <u>የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ</u>**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 13 በአቶ ያፌት ኃይሌ አሰግዴ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር --------- ባለቤትነት የይዞታ ካርታ ቁጥር ሊዝ51/16035/03 በሴሪ ቁጥር 015869 የተሰጠበት ቀን 27/05/2003 ዓ.ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደጠፋባቸው በቀን 04/02/2018 ዓ.ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ 30 ቀን ውስጥ በይዞታው መብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ያገኘ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ሲለሆነ የይዞታ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣላቸው ሲሆን ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ለአመልካቹ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ የን/ስ/ላ/ክ/ከ ትምህርት መምሪያ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 05 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር የን/ስ/ላ/ክ/ከ ሊዝ ጨ001/97 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በሳንቶስ ሪል እስቴት ሀላ/የተ/የግ/ማ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር -------- የመሬት ይዞታ ካርታ ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000040202021 የሆነው የይዞታ ማረጋጋጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን /ዘጠና ቀን/ ድረስ ጽ/ቤታችን ቀርበው እንዲያሳውቁ ካልቀረቡ ግን በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቂርቆስ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ማክሮ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ካርታ ቁጥር AA000060807902 በሴሪ ቁጥር 010242 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፡- <u>የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ</u>**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እነደተሞከረው በየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 13 በወ/ት ማርያማዊት ኃይሌ አሰግዴ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር -------- ባለቤትነት የይዞታ ካርታ ቁጥር ሊዝ51/16058/03 በሴሪ ቁጥር 015867 የተሰጠበት ቀን 01/06/2003 ዓ.ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደጠፋባቸው በቀን 04/02/2018 ዓ.ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ በ30 ቀን ውስጥ በይዞታው መብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ያገኘ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ የይዞታ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣላቸው ሲሆን ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ለአመልካቹ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ለመኖሪያ አገልግሎት በካርታ ቁጥር 18/72/10.525/00 በሴሪ ቁጥር 093231 በእጥፍወርቅ ወልደየስ ጉርሙ ተሰጥቷቸው የነበረው ማህደር ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ማህደር እንደሚከፈትላቸው እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በእዮብ ተስፋዬ ገዛኸኝ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 14 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA0000801202310103ll በሴሪ ቁጥሩ 0188532 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ለሦስተኛ (3) ጊዜ የወጣ ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያን ይመለከታል

መለያ ቁጥር 03/2018ዓ.ም

በልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የህዳሴ ልደታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለ2018 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውሉ ለደንብ ልብስ ስፌት፣ ለኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ ለፈርኒቸር እቃዎች፣ ስቴሽነሪ/የፅህፈት መሳሪያ እቃዎች፣ ልዩ ልዩ መሳሪያዎች፣ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ ከዚህ በታች በዝርዝር የቀረቡትን መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች በሙሉ በጨረታው እንድትሳተፉ እንጋብዛለን፡፡

1. አገልግሎቱን እና እቃውን በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል ብቃት ያለው ሕጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸው እና 2018 ዓ.ም የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፡፡
2. ተጫራቾች በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡና የምስክር ወረቀቱን ኮፒ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች በተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት ተመዝጋቢ የሆኑና ለዚህም የተመዘገቡበትን ኮፒ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋጋ፡-

ሎት 1- አላቂ የትምህርት እቃዎች 5000
ሎት 2- የቢሮ ፈርኒቸር እቃዎች 5000
ሎት 3- ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች 100000
ሎት 4- ልዩ ልዩ ማሳሪያዎች 5000
ሎት 5- ስፌት 3000

5. ተጫራቾች የጨረታውን ዝርዝር ሰነድ በማይመለስ ብር 200.00/ሁለት መቶ ብር ብቻ/ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ጎማ ቁጠባ ፊት ለፊት ከሚገኘው ህዳሴ ልደታ 2ኛ/ደረጃ ት/ቤት መውሰድ ይችላሉ፡፡
6. ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ናሙና ለሚቀርብላቸው እቃዎች ናሙና የቀረቡ ብቻ የሚወዳደሩ ሲሆን ለቋሚ እቃዎችን በስፔስፊኬሽን መሰረት ይሆናል፡፡
7. ተጫራቾች በገዙበት የጨረታ ሰነድ ላይ በተዘጋጀው የዋጋ ዝርዝር መሙያ ላይ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው፡፡ በሌላ ሰነድ የሞሉ ተቀባይነት የለውም፡፡
8. ባቀረቡት የዋጋ ዝርዝር ላይ ቫት ማካተት አለባቸዉ፡፡
9. ት/ቤቱ በሚገዛው እቃ ላይ 20% የመጨመርና የመቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነዉ፡፡
10. ጨረታዉ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ለአስር(10) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የሚጫረቱበትን የመወዳደሪያ ዋጋ ሞልተው በታሸገ ፖስታ ት/ቤቱ ባዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸዉ፡፡
11. በአስረኛው ቀን እስከ 11:30ሰዓት ብቻ ሰነዱ ይገባል፡፡ በአስራ አንደኛው ቀን በ4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ሳጥኑ ይከፈታል፡፡ ጨረታው የሚከፈትበት 11ኛው ቀን የበዓል ወይም ቅዳሜና እሁድ ከሆነ በቀጣይ ባለው የስራ ቀን ይከፈታል፡፡
12. የጨረታ አሸናፊ የሚሆነው በሞላው ነጠላ ዋጋ ነው፡፡
13. አሸናፊዎች ያሸነፉትን እቃ በራሳቸው ትራንስፖርት እስከ ት/ቤቱ ማቅረብ አለባቸው፡፡
14. የጨረታው አሸናፊ ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት /5/ የስራ ቀናት ውስጥ የውል ማስከበሪያ ባሸነፈበት እቃ ላይ 10% CPO ማስያዝ የሚችል መሆን አለበት፡፡

**ማሳሰቢያ**

- ት/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነዉ፡፡
- ሁሉም እቃ አዲስ መሆን አለበት፡፡
- ናሙና እስከ 10 ቀን ብቻ የምንቀበል ይሆናል፡፡
- ተጫራቾች ዝርዝር መረጃ ካስፈለገዎት በአካል በመምጣት ያነጋግሩን፡፡

**አድራሻ፡-** በልደታ ክ/ከ/ወረዳ 05 ጎማ ቁጠባ ፊት ለፊት ወይም ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፊት ለፊት

**በልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የህዳሴ ልደታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት**
**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ልደታ ክ/ከተማ ት/ፅ/ቤት የህዳሴ ልደታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት**

---

በዮዲት ታደሰ አብዲሳ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ4/16/2/9/2299/19374/01 የተሰጠበት ቀን 23/4/2005 ዓ.ም የቦታው ስፋት 509 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 03 የሆነው መኖሪያ ቤት በዮዲት ታደሰ አብዲሳ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ4/16/2/9/2299/19374/01 የተሰጠበት ቀን 23/4/2005 ዓ.ም የቦታው ስፋት 509 ካ.ሜ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታውን (ቤቱን) በዕዳ ይገዤዋለሁ፣ አስይገዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ መሆኑን እየገለፅን የማስታወቂያው ወጪ በባለጉዳዩ የሚሸፈን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በሊዛ ሸዋዓለም ህጋዊ ወኪል በቀን 04/07/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በካርታ ቁጥር ሊ.ዝ.ድ/0400/0230 የተሰጠበት ቀን 21/09/1992 ዓ.ም የቦታው ስፋት 290 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 10 የሆነው መኖሪያ ቤት በሊዛ ሸዋዓለም ህጋዊ ወኪል በቀን 04/07/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በካርታ ቁጥር ሊ.ዝ.ድ/0400/0230 የተሰጠበት ቀን 21/09/1992 ዓ.ም የቦታው ስፋት 290 ካ.ሜ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታውን (ቤቱን) በዕዳ ይገዤዋለሁ፣ አስይገዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ መሆኑን እየገለፅን የማስታወቂያው ወጪ በባለጉዳዩ የሚሸፈን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 በፋሲል ጥላሁን በየነ እና ቢንያም አለሙ ዳቢ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የ ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA00006081O149 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ / ይገዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንዲሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/**ቤት

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ እዮብ ተስፋዬ ገዛኸኝ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 14 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA000080120231010417 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ እዮብ ተስፋዬ ገዛኸኝ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 14 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA000080120231010207 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ እዮብ ተስፋዬ ገዛኸኝ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 14 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA000080120231010313 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የካርታ ቁጥር የካ102/186820/07 በሴሪ ቁጥር 059432 በጌታነህ መኮንን ስም ያለውን ይዞታ አስመልክቶ ይህን ይዞታ በእዳ እገዳ ይገዤዋለሁ የሚል ተቋምም ሆነ ግለሰብ ወይም ይዞታው ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያለው አካል ካለ በ30 (ሰላሳ) ቀን ውስጥ በየካ ክ/ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ ካርታቸውን እንዲያስረክበን እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ8/19/4/3/10471/13949/01 ስም ሴሪ ቁጥር 1450982 በብርትኳን ከበደ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ ሰለሞን ፅጌ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 015524 ሴሪ ቁጥር 000769 የይዞታ ስፋት 94.64 ካ.ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወ/መ/10/20603/18 በቀን 07/07/18 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይገዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአማኑኤል ተመስገን ያኖሬ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA0000801111177 በሴሪ ቁጥሩ 0210345 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ እዮብ ተስፋዬ ገዛኸኝ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 14 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA000080120231010208 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ቀሪ ጨዋታዎችን የሚያስናፍቀው ተወዳጁ ሊግ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ የ2025/26 የውድድር ዘመን ወደ ማጠናቀቂያው ምዕራፍ ተቃርቧል። ቀሪዎቹ ስምንት ጨዋታዎች በደረጃ ሰንጠረዡ አናት፣ መሃልና ግርጌ የሚገኙ ክለቦችን እጣ ፈንታ የሚወስኑ የሞት ሽረት ፍልሚያዎች የሚስተናገዱባቸው ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የዘንድሮው የፕሪሚየር ሊግ ጉዞ ካለፉት ዓመታት በተለየ መልኩ እጅግ ተለዋዋጭና አስገራሚ ክስተቶች የታዩበት ሆኖ መካሄዱን ቀጥሏል። ገና ከጅምሩ አንስቶ የሊጉ ግዙፍ ክለቦች ነጥቦችን ሲጥሉና በአንጻሩ መጠነኛ ግምት የተሰጣቸው ቡድኖች ደግሞ ድሎችን ሲያስመዘግቡ ታይቷል፡፡ በተለይም የማጥቃት እግር ኳስ የበላይነት በታየባቸው ያለፉት ወራት፣ በርካታ ግቦች የተቆጠሩባቸውና እስከ መጨረሻው ደቂቃ ድረስ አሸናፊው የማይታወቅባቸው ጨዋታዎች ልዩ የስታዲየም ድባብና ስሜት ሲፈጥሩ ቆይተዋል። ይህ ሂደት ደግሞ ሊጉን በዓለም ላይ ካሉ ውድድሮች ሁሉ ይበልጥ ተመራጭና የማይገመት እንዲሆን አድርጎታል።

ወሳኝ ምዕራፍ ላይ በሚገኘው የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ አናት ላይ ያለው ሁኔታ ከአስር ያነሱ የጨዋታ ሳምንታት በቀሩበት በዚህ ወቅት የዋንጫ ፉክክሩ፣ ለሻምፒዮንስ ሊግ ቦታ የሚደረገው ትግል እና ከወራጅ ቀጣና ለመውጣት የሚደረገው ፍልሚያ ውጥረት የነገሰበት እና ትኩረትን የሳበ ሆኗል፡፡ በተለይ የሰሜን ለንደኑ ክለብ አርሰናል አንድ ቀሪ ጨዋታ ካለው ማንቸስተር ሲቲ በዘጠኝ ነጥብ ርቆ ሊጉን እየመራ ቢሆንም የሊጉ አስገራሚ ተለዋዋጭነት ዋንጫው ወደየት እንደሚያመራ ለመገመት ከባድ ያደርገዋል፡፡

በተለይ አርሰናል እና ማንቸስተር ሲቲ በቅርቡ እርስ በእርስ የሚገናኙበት የፕሪሚየር ሊግ ጨዋታ የዋንጫውን አሸናፊ የመወሰን ትርጉም ያለው መርሃ ግብር ቢሆንም በወረቀት ላይ በአንጻራዊነት የአርሰናል ቀሪ ጨዋታዎች ቀላል ይመስላሉ፡፡ በተጨማሪም መድፈኞቹ በሊጉ ከሚያደርጓቸው ቀጣይ አምስት ጨዋታዎች አራቱ በኤምሬትስ የሚደረጉ መሆናቸው ይበልጥ ወደ ዋንጫው ለመቅረብ ዕድል የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡ በተለይ ደግሞ በዚህ ዓመት በሜዳው በአንድ ጨዋታ ብቻ የተሸነፈው አርሰናል ቀጣይ ከሚያደርጋቸው አምስት ጨዋታዎች አራቱን በሜዳው ማድረጉ ብቻ ሳይሆን የሚያገኛቸው ቡድኖች መካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወይም የመውረድ ስጋት የሌለባቸው መሆኑ ሌላ ዕድል የሚሰጠው ሆኗል፡፡

በተቃራኒው የማንቸስተር ሲቲ ቀጣይ አምስት ጨዋታዎች ከባድ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ማንቸስተር ሲቲ ቀጣይ ከሚያርጋቸው አምስት ጨዋታዎች መካከል ወደ ምዕራብ ለንደን አምርቶ ከቼልሲ የሚደረገውን ጨምሮ አራቱ ከሜዳው ውጪ የሚያደርጋቸው ናቸው። በተጨማሪም በሜዳው የሚያደርገው አንዱ ጨዋታም ከቀጥተኛ የዋንጫ ተፎካካሪው አርሰናል ጋር ነው፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ቀሪ ጨዋታዎች ለአሸናፊነት፣ የሻምፒዮንስ ሊግ ቦታን ለመያዝና ላለመውረድ የሚደረገው ፍልሚያ ትኩረትን የሳበ ሆኗል

ሌላኛው በሻምፒዮንስ ሊግ ለመሳተፍ የሚደረገው ጉዞ ነው፡፡ በዚህ ዓመትም አምስተኛ ደረጃን ይዞ የሚያጠናቅቀው ቡድን በሻምፒዮንስ ሊግ የመሳተፍ ዕድል ያለው በመሆኑ፣ ማንቸስተር ዩናይትድ፣ አስቶን ቪላ፣ ቼልሲ እና ሊቨርፑል ይሄንን ደረጃ ለማግኘት ትልቅ ፉክክር የሚያደርጉበት ይሆናል። በተለይ በእያንዳንዳቸው መካከል ያለው የነጥብ ልዩነት የተቀራረበ መሆኑ እና እርስ በእርስ የሚገናኙ መሆናቸው ቀሪ መርሃ ግብሮች ከዋንጫው ፉክክር እኩል እንዲጠበቁ ያደርገቸዋል፡፡ 4ኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠው አስቶን ቪላ በቀጣይ የሚያርጋቸው ስድስት ተከታታይ ጨዋታዎች ከ7ኛ ደረጃ በታች ያሉ በመሆናቸው በአንጻራዊነት ቀላል የሚባሉ ናቸው፡፡

ከማይክል ካሪክ በኋላ በብዙ የተቀየረው ማንቸስተር ዩናይትድ ቀጣይ ከሚያርጋቸው 6 ጨዋታዎች ሦስቱን ለሻምፒዮንስ ሊግ ቦታ የሚፋለምባቸው መሆናቸው ፈተናውን ከባድ ያደርግበታል፡፡ ከቼልሲ እና ሊቨርፑል ቀሪ ተጋጣሚዎቹ ሲሆኑ ሌላኛው ከባድ ፈተና የሚጠብቀው ቼልሲ ከቀጣይ ስድስት ጨዋታዎች ማንቸስተር ዩናይትድ እና ማንቸስተር ሲቲን በተከታታይ የሚያገኝበት ይጠቀሳል፡፡ በአንጻራዊነት ሊቨርፑል እድሉን መጠቀም ከቻለ ቢያንስ በወረቀት ላይ ከባድ የሚባሉ አይደሉም፡፡

ላለመውረድ በሚደረገው ትግል ወልቭስ እና በርንሌይ የተለየ ተዓምር ካልተፈጠረ በስተቀር በሊጉ የመቆየታቸው ነገር ያበቃለት ይመስላል። ነገር ግን ሊድስ ዩናይትድ፣ ቶተንሃም፣ ኖቲንግሃም ፎረስት እና ዌስትሃም ካላቸው የነጥብ መቀራረብ የተነሳ በሊጉ ለመቆየት የሚፋለሙበት ነው፡፡ 15ኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሊድስ ዩናይትድ ከሌሎቹ አንጻር ቀለል ያሉ ተጋጣሚዎች አሉት፡፡ በተቃራኒው ወራጅ ቀጣናው ውስጥ የሚገኘው ዌስትሀም ምንም እንኳን በቅርቡ እየተሻሻለ ቢመጣም ከማንቸስተር ሲቲ፣ ከአስቶን ቪላ እና ከአርሰናል ያልጨረሳቸው የቤት ስራዎች መኖራቸው በሊጉ የመቆየቱን ጉዳይ እጅግ ፈታኝ ያደርግበታል፡፡

ድንገት ራሱን የመውረድ ስጋት ውስጥ ያገኘው ቶተንሃም ሆትስፐርም ከዌስትሃም በአንድ ነጥብ ከፍ ብሎ የተቀመጠ ሲሆን፣ ባለፉት 11 ተከታታይ የሊግ ጨዋታዎች አለማሸነፉ የመትረፉን ነገር ጥያቄ ውስጥ ከቶታል፡፡ የሰሜን ለንደኑ ክለብ ከአስቶን ቪላ እና ከቼልሲ እንዲሁም ቀጥተኛ ተፎካካሪዎቹ ከሆኑት ላለመውረድ ከሚታገሉት ቡድኖች ጨዋታ ያለው መሆኑ ለመቆየት ከባድ የቤት ስራም ይጠብቀዋል፡፡

ላለመውረድ የሚደረገው ትግል በሊጉ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ጥብቅ ፍልሚያ እንደሚሆን ይገመታል። በደረጃ ሰንጠረዡ ግርጌ የሚገኙት አምስት ክለቦች በነጥብ ያላቸው መቀራረብ፣ እያንዳንዱን ጨዋታ እንደ ዋንጫ ፍጻሜ እንዲመለከቱት ያደርጋቸዋል። በመጨረሻም፣ የግል ክብረወሰኖች ሰባሪው ኤርሊንግ ሃላንድ በ38 ጨዋታዎች ውስጥ ያስመዘገበውን የጎል ብዛት ራሱ የመስበር ዕድሉ ሰፊ እንደሆነ ኦፕታ (Opta) ያመላክታል።

በአጠቃላይ፣ እነዚህ ስምንት ሳምንታት በታክቲክ ብስለት፣ በአካላዊ ብቃትና በስነ-ልቦና ጥንካሬ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው፣ የ2025/26 የውድድር ዘመን ማሳረጊያ በታሪክ ማህደር ውስጥ በደመቀ ቀለም እንደሚሰፍር ጥርጥር የለውም።

የ2025/26 የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ የውድድር ዘመን በሜዳ ላይ ድርጊቶች ብቻ ሳይሆን በቴክኖሎጂና በስታቲስቲክሳዊ መረጃዎችም የታሪክ መፃህፍትን እያደሰ ይገኛል። እንደ ኦፕታ መረጃ የዘንድሮው የውድድር ዓመት በሊጉ ታሪክ ከፍተኛው የጨዋታ ፍጥነት እና የተጫዋቾች የሩጫ ርቀት (High-intensity sprints) የተመዘገበበት ሲሆን፣ ይህም ካለፉት ሁለት ዓመታት በአማካይ በ12 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። በተለይም አሰልጣኞች ከመከላከል ይልቅ ለአጥቂ እግር ኳስ በሰጡት ቅድሚያ ምክንያት፣ በጨዋታው መገባደጃ (ከ90ኛው ደቂቃ በኋላ) የሚቆጠሩ ወሳኝ ግቦች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ የሊጉን አስገራሚ ተለዋዋጭነትና የቡድኖችን እስከመጨረሻው የመታገል መንፈስ በግልጽ ያሳያል።

በሌላ በኩል፣ የዘንድሮው የውድድር ዓመት በከፊል አውቶማቲክ የጨዋታ ውጭ መቆጣጠሪያ (Semi-automated Offside Technology) ስራ ላይ መዋልና በቪ.ኤ.አር (VAR) ውሳኔዎች ግልፅነት ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች የውድድሩን ፍሰት መልክ ቀይረውታል። እንደ ፕሪሚየር ሊግ ዳታ ሴንተር መረጃ ከሆነ፣ በዘንድሮው የውድድር ዘመን በሜዳቸው ነጥብ የማይጥሉ ክለቦች ቁጥር መጨመሩና እንደ ትራንስፈርማርኬት ባሉ ምንጮች የሚገለጸው የወጣት ተጫዋቾች የገበያ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ማደግ፣ የሊጉን የፉክክር ሚዛን ወደ አዲስ ምዕራፍ አሸጋግሮታል። እነዚህ ክስተቶች ተዳምረው የ2025/26ን የውድድር ዘመን በፍትሐዊነትና በከፍተኛ ፉክክር የታጀበ ከማድረጋቸው ባለፈ፣ በዓለም ዙሪያ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ተመልካቾችን የሳበ ታላቅ ስፖርታዊ ድራማ አድርገውታል።

የ2025/26 የፕሪሚየር ሊግ የውድድር ዘመን ማሳረጊያ በሜዳ ላይ ከሚታየው ብርቱ ፉክክር ባለፈ፣ በቴክኖሎጂና በስታቲስቲክሳዊ መረጃዎች የታጀበ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እየፃፈ ይገኛል። ቀሪዎቹ ስምንት ጨዋታዎች ተራ እግር ኳስ ሳይሆኑ፣ የክለቦች የዓመታት ድካም ፍሬ የሚታይባቸውና የደጋፊዎች የልብ ትርታ የሚለካባቸው ወሳኝ ደቂቃዎች ናቸው። ዋንጫው ወደ ሰሜን ለንደን ያመራል ወይንስ በማንቸስተር ሰማይ ስር ይቆያል? ለሻምፒዮንስ ሊግ የሚደረገው ሽሚያና ላለመውረድ የሚደረገው የሞት ሽረት ትግልስ በማን ድል አድራጊነት ይጠናቀቃል? መልሱን ለማግኘት የሜዳ ላይ ድራማውን አብረን መከታተላችንን እንቀጥላለን።

**የዘንድሮው የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ጉዞ ካለፉት ዓመታት በተለየ መልኩ እጅግ ተለዋዋጭና አስገራሚ ክስተቶች የታዩበት ነው፤ ባለፉት ወራት የተደረጉ ጨዋታዎች እስከ መጨረሻው ደቂቃ ድረስ አሸናፊው የማይታወቅባቸው ሆነው ቆይተዋል፤ ሂደቱ ሊጉን ይበልጥ ተመራጭና የማይገመት እንዲሆን አድርጎታል**


ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም
ቴሌብር
telebirr
ዒድ ሙባረክ
Eid
MUBARAK
በፍቅር፣ በደስታ፣ በመተሳሰብ እና
በአብሮነት የተሞላ የዒድ-አል-ፊጥር በዓል
እንዲሆንልዎ እንመኛለን፡፡